# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪው መጽሐፍ

3ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ትምህርት ቢሮ

የግብረ ገብ ትምህርት የተማሪ መፅሐፍ ሶስተኛ ክፍል

# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪው መጽሐፍ

ቅድሚያ ይስጡ

3ኛ ክፍል



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ትምህርት ቢሮ

# ይህ መጽሐፍ በጥንቃቄ ይያዝ!



ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው፡፡ ስለዚህም እንዳይጎዳ ወይም እንዳይጠፋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ይረዷችሁ ዘንድ የሚከተሉትን 10 ነጥቦች አስተውሉ፡፡

1. መጽሐፉን እንደ ፕላስቲክ፣ ጋዜጣ እና በመሳሰሉ ቁሶች መሸፈን፣
2. መጽሐፉን ንጹህ እና ደረቅ ቦታ ማስቀመጥ፣
3. መጽሐፉን በሚጠቀሙበትጊዜ እጅዎት ንጹህ መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በመጽሐፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገጾች ላይ አለመጻፍ፣
5. ገጾችን ከማጠፍ ይልቅ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድለምልክት መጠቀም፣
6. ማናቸውንም ምስሎች ወይም ገጾችን ፈጽሞ አለመቅደድ፣
7. ማናቸውንም የተቀደዱ ገጾች መጠገን፣
8. መጽሐፉን በቦርሳ ውስጥ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፣
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ሲያውሱ በጥንቃቄ ማቀበል፣
10. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቀሙ፤ መጽሐፉን በጀርባ ሽፋኑ በኩል ማስቀመጥ ከዚያም በአንድ ጊዜ ውስን ገጾችን መግለጽ፤ እንዲሁም የመጽሐፉን ጠርዞች በትንሹ ጫንጫን ማድረግ፡፡ ይህም የመጽሐፉ ሽፋን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ይረዳል፡፡

# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪ መፅሐፍ

## የ3ኛ ክፍል


አዘጋጆች ኪዳኔ ኃይሉ ደሜ (M.Ed)

ማሩ ማቲዎስ ኤርቤቶ (MA)

አርታዒዎች ዳኘ ጥላሁን አሰፋ (MA)

ጃንቦ ጉድሩ ፊጋ (MA)

ዶ/ር እባቡ ተፈራ አዱኛ (አሶሼት ፕሮፌሰር) (PHD)

ሰዓሊ አቶ ዋሲሁን ዳኘ ምህረቱ (M.sc)

ሌይአውት ዲዛይነር መስፍን አብርሃም (B.sc) (አመሳክሮ የሰራው)

አቶ ዳዊት ደጀኔ ቢቂላ (M.sc)

ተርጓሚዎች ዋሲሁን አስማረ (M.A)

ዳግማዊት ይርጋ (M.A)

አርታኢና ገምጋሚ በላይ በለጠ (M.A)

አስተባባሪ ጌታቸው ታለማ (M.A)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# ምስጋና

በመጀመሪያ የታተመው--------2022 በፌደራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የትምህርት ጥራትና ማሻሻያ መረሃ-ግብር ለፍትሃዊነት (GEQIP-E) ፤በአለም ባንክ የሚደገፈው የእንግሊዝ አለም አቀፍ ዲፓርትመንት አሁን ከውጭ የጋራ ሀብትና ልማት ቢሮ ጋር የተቀላቀለው /DFID-, የፊንላንድ የውጭ ጉዳየይ ሚኒስቴር የሮያል የኖርወይ ኢምባሲ፤ የተባብሩት መንግስታት ህጻናት ፈንድ /UNICEF)፡ አለም አቀፍ የትምህቸት አጋርነትና የዴንማርክ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር (GPE)፤ እና በብዙ ለጋሽ (ትረስትፈንድ) በኩል ነው፡፡

© 2022 መብቱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የተረጋገጠ ነው፡፡ የጸሀፊው የሞራል መብቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ የመምህሩ መማሪያ መጽሐፍ ክፍል አስቀድሞ ከትምህርት ሚኒስቴር የጽሁፍ ፍቃድ ወይም ፍቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በማንኛም መልኩ በኤሌክትሮኒክስ፣ ሜካኒካል፣ ማግኔቲክ፣ ፎቶ ኮፒ፣ ቅጂ ወይም በሌላ መልኩ ተባዝቶ ማስተላለፍ አይቻልም፡፡ የኢትጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የቅጂ መብትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ

የትምህርት ሚኒስቴር ይህንን የመምሩ መማርያ መጽሐፍ ለማተም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፉትን በርካታ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን እና ሌሎች አካላትን ማመስገን ይፈልጋል፡፡ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ፣ ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ እና ከጅማ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ልዩ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በባለቤቶቻቸው ፈቃድ ጥቅም ላይ የዋሉ የቅጂ መብት ያላቸው ቁሳቁሶች ናቸው፡፡ በቅጂ መብት የተጠበቁ ነገሮች ያልተጠቀሱ ወይም ያለአግባብ ያልተጠቀሱ ከሆነ እባኮትን የትምህርት ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤት አራት ኪሎ (ፖ.ሳ.ቁ 1367) ፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ያነጋግሩ፡፡

የታተመው: XXXXXX
ፖ.ሳ.ቁ. XXXXXX
በትምህርት ሚኒስተር ስር የስምምነት ቁ. XXXXXX
ISBN: 978-999944-2-046-9

# ማውጫ

ይዘት ገፅ


መግቢያ........................................................

ምዕራፍ አንድ: ሰብዓዊነትን ማክበር........................................1

1: ሰብዓዊነት........................................................1

- 1.2: ሰብዓዊ ክብር........................................................4
- 1.2.1 ሰብዓዊነትን ማክበር እና ያለው ጠቀሜታ....................................5
- 1.3: የሰብዓዊነት መሰረታዊ መገለጫዎች....................................6
  - 1.3.1 ፍቅር........................................................6
  - 1.3.2 ርህራሄ እና ሀዘኔታ........................................................8
  - 1.3.3 በጎ አድራጎት........................................................10
  - 1.3.4 በጎ ፈቃደኝነት........................................................11
  - 1.3.5 ጨዋነት........................................................12
  - 1.3.6 ወንድማማችነት........................................................13
  - 1.3.7 ታጋሽነት........................................................14
  - 1.3.8 ሰላም........................................................15

የምዕራፉ ማጠለያ........................................................17

የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች........................................................17

ምዕራፍ ሁለት: ሌሎችን ማክበር........................................................20

- 2.1:ክብር........................................................21
- 2.2: ሌሎችን ማክበር........................................................22
- 2.3 ሌሎችን የማክበር አስፈላጊነት........................................................23
  - 2.3.1 ታላለቆችን ማክበር........................................................23
  - 2.3.2 የእምነት አባቶችን ማክበር........................................................25
  - 2.3.3 መምህራንን ማክበር........................................................26
  - 2.3.4 ቤተሰብን ማክበር........................................................27
  - 2.3.5 ጎረቤትን ማክበር........................................................28
  - 2.3.6 የክፍል ጓደኞችን ማክበር........................................................29
- 2.4 የተከበሩ ሰዎች ባህሪያት........................................................30
- 2.5 ሌሎችን ክብር መንፈግ እና የሚያመጣው ተጽዕኖ........................................31

የምዕራፉ ማጠቃለያ........................................................32

የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች........................................................33

ምዕራፍ ሦስት: እኩልነት ....................................................................34
ክፍለ-ትምህርት 3.1: እኩልነት ምንድነው....................................................35
ክፍለ-ትምህርት3.2: እኩልነት በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ .............37
- 3.2.1: የፆታ እኩልነት....................................................................37
- 3.2.2: የቋንቋ እኩልነት..................................................................39
- 3.2.3 የሃይማኖት እኩልነት..............................................................39
- 3.2.4 የባህል እኩልነት ....................................................................41
- 3.3 ሰዎችን በእኩል የማየት አስፈላጊነት............................................42
- 3.4 እኩል ያለመሆን አሉታዊ ውጤቶቹ................................................43

የምዕራፉ ማጠቃለያ..................................................................................44
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች...............................................................45
ምዕራፍ አራት: ጤናማ ማህበራዊ ህይወት......................................................48
- ውየምዕራፉ ማጠቃለያ..........................................................................53

የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች...............................................................54
ምዕራፍ አምስት: መተባበር እና በቡድን መስራት.............................................56
- 5.1: መተባበር እና በቡድን መስራት ..............................................57
- 5.2: የመተባበር እና በቡድን የመስራት ባህል....................................57

5.2.1 ለማህበረሰቡ...............................................................................57
5.2.2. በትምህርት ቤት በቡድን መስራት..................................................58
- 5.3. የመተባበር እና በቡድን የመስራት ባህል መርሆች..........................59
- 5.4 የመተባበር እና በቡድን የመስራት ባህል ክህሎቶች.........................60

5.4.1 የሌሎችን ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ መሆን...........................................60
5.4.2 ተግባቦት.......................................................................................60
5.4.3 አደረጃጀት....................................................................................61
5.4.4 ክርክር..........................................................................................62
5.4.5 ጊዜን በአግባቡ መጠቀም.................................................................63
5.4.6 የመተባበር እና በቡድን የመስራት ባህል ጠቀሜታዎች.........................64
የምዕራፉ ማጠቃለያ..................................................................................65
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች...............................................................66

ምዕራፍ ስድስት  የባህል ብዝሃነት ..........67
- 6.1 የብዝሃ ባህል ትርጉም ..........68
- 6.2 የብዝሃ-ባህል ዓይነቶች በማህበረሰብ ውስጥ..........68
  - 6.2.1 ..........69
  - 6.2.2 የባህል አልባሳት..........69
  - 6.2.3 ባህላዊ ሙዚቃ..........70
  - 6.2.4 ባህላዊ ምግብ..........70
  - 6.2.5 የሰርግ ባህል..........71
- 6.3 ብዝሃ-ባህልን የማስተናገድ ጠቀሜታ..........71
- 6.4 ብዝሃ-ባህልን ማስተናገጃ መንገዶች..........72

የምዕራፉ ማጠቃለያ..........73
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች..........74

# መግቢያ

የሰው ልጅ ምክንያታዊ እንስሳ መሆኑ ግልጽና የሚታወቅ ነው፡፡ ከሌሎች ፍጥረታት በንፅፅር የሰው ልጆች ልዩ መሆን ከባህሪያቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከፍጥረታት ሁሉ የተለየ ባህሪ ያላቸው ሰው ልጆች ብቻ ናቸው፡፡ ባህሪ ሰዎች ያስቀመጧቸውን ግቦች በራሳቸው ለማሳካት ሲሉ ራሳቸውን ለማነፅ የሚያዳብሩት ነገር ነው፡፡ ባህሪን ለመላበስ ሰዎች ከምክንያትና ስነ-ምግባራዊ መርህ የሚመነጭ ተግባራዊ መርህ ሊኖራቸው ይገባል፡፡የሰው ልጅ ስነ-ባህሪ ከራሱ አስተሳሰብ የሚወለድ እስከሆነ ድረስ ሌሎችን በመምሰል የመልካም ባህሪ ባለቤት መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ ከሌሎች ፍጥረታቶች አኳያ የሰው ልጆች የተለዩ መሆናቸው በምድር ላይ የአመክንዮ እና የ ህሊና መኖርን አመላካች ነው፡፡ሰዎች የማንነት ባህሪያቸውን የሚያገኙት በአዕምሮ መሪነት ነው፡፡

የሰው ልጅ ዝርያው በማህበረሰብ ውስጥ መኖር እንዲችል ትዕዛዝን፣ ስልጠናን እና ትምህርትን መስጠት የሚችል ብቸኛው ፍጡር ነው፡፡የ ሰው ልጅ ባህሪና ሌሎች ችሎታዎች በትምርት እንጂ በውርስ ሊገኙ የሚችሉ አይደሉም፡፡የሰው ልጅ የመማር ችሎታእጂግ ጠቃሚው ባህሪ ነው፡፡ይህ ባህሪ የሰው ልጅ አጠቃላይ እድገቱንና ስልጣኔውን መቀጠል የሚያስችለው ነው፡፡የሰው ልጅየቱንም ያህል ቢማርና ቢሰለጥንም ግብረ-ገብ ይሆን ዘንድ ደግሞ ግድ ይለዋል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በጎነት ከውልደት ጀምሮ ሊኖር የሚችል እሴት አይደለም፡፡በጎነት በተለያዩ መንገዶች መገኘት አለበት፡፡ እውነት ነው የሰው ልጇ የሞራል ግደታዎችን የመወጣት ብቃት አለው፡፡ በጎነት ሊገኝ ወይም ሊደረስበት የሚችል ነገር ግን ተፈጥሯዊ ያልሆነ ነገር ነው፡፡ በጎነት በጎ ባህሪን ለማዳበር በስልጠናዎች መደገፍ የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በሌላ አገላለፅ ግብረ-ገብነት ከሰው ልጅ የእለት ተዕለት ክንውኖች የሚወረስ ማህበራዊ ተግባር ነው፡፡ ከእናንተ አንዳችሁ በዓለም ላይ ብቸኛው ሰው ብትሆኑ ኖር ስነ-ምግባር አያስፈልግም ነበር፡፡ግለሰቦች ያለ ማህበራዊ ከባቢ የሰብዐዊነትን መገለጫዎች ሊያገኙ አይችሉም፡፡እናም ሰብዓዊነት የተላበሱ ሰዎች ከሌሉ የሰው ማህበራዊነት ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ባህሪዎች እርስ በርሳቸው የሚሞላሉ ናቸው፡፡

በተጨማሪም ስነ-ምግባር/ግብረገብነት ማለት እውነትን በመፈለግ ውስብስብ በሆነ ዓለም ውስጥ እንደት አብሮ መኖር እንደሚቻል መረዳት ነው፡፡ስነ-ምግባር/ግብረገብነት ማለት የማህበረሰብ ቁጥጥር ዓይነት ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ መደበኛ፣ትክክለኛ ወይም የሚጠበቁ የባህሪ ማሳያ መንገዶችን ገልጧል፡፡ስለዚህ እነዚህ ተስፋዎች ማህበረሰቡ በተረጋጋ ሁኔታ እንዲሰራ የሚያግዙ የባህሪ መመሪያዎች ሆነው የሚያገለግሉ ማበራዊ ደንቦች ናቸው፡፡ማንኛውም ማህበረሰብ በህይወት እንዲኖር ከተፈለገ ማህበራዊ ደንቦቹን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ አለበት፡፡ሰዎች እስካልተማሯቸው ድረስ ማህበራዊ ደንቦችን ማክበር እንደማይቻል የሚታወቅ ነው፡፡ እዚጋ ታዳጊዎችን ደንቦች ምን እንደሆኑ እና በምንም መልኩ መጣስ እንደሌለባቸው በማስተማር ረገድ ማህበራዊነት ማዕከላዊ ሚና ይጫወታል፡፡ሰዎች ማህራዊ ደንቦቻቸውን ከግብረ-ገባዊ ግደታ ጋር ይማራሉ፡፡በሌላ አገላለፅ ሰዎች የማህበረሰባቸውን ማህራዊ ደንቦች ሲማሩ እነርሱን ለመታዘዝ የግብረ-ገብነት አስፈላጊነትንም በውስጣቸው ያሰርፃሉ፡፡ ይኸውም በሰዎች አኗኗር እና ልማድ የተካተተ የዕለት ተዕለት ተግባር ነው፡፡ ማህበራዊ ደንብ ማለት የህብረተሰቡ የባህሪ መመሪያ(የስነ-ምግባር ደንብ) ነው፡፡ ስነ-ምግባር/ግብረ-ገብነት በአብዛኛው ሁሉም ሰው የሚከተላቸው ከሆነ ሁሉም ሰው ሊሻሻልባቸው የሚችሉ ህገ-ደንቦችን ያካተተ ነው፡፡ ነፃነታቸውን የሚገድቡ ቢሆኑም እንኳ ሰዎች እነዚህን ህገ-ደንቦች መከተል

አለባቸው፡፡በዚህ እውነታ ምክንያት እነዚህ ህገ-ደንቦች የበለጠ ነፃነትን እና ደህንነትን ያበረታታሉ፡፡ በአጠቃላይ ስነ-ምግባር እነዚህ አምስት ዓላማዎች ያሉት ይመስላል፡ 1.ማህበረሰብ እንዳይለያይ ለማድረግ 2.የሰዎችን ሰቆቃ ለማሻሻል/ለማቅለል 3.የሰዎችን መሻሻል/እድገት ለማስተዋወቅ 4.የጥቅም ግጭቶችን ፍትሐዊ እና ስርዓታዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት 5. ምስጋና እና ወቀሳ፣ሽልማት እና ቅጣት፣ እና ጥፋተኝነትን ለመመደብ፡ ፡አስተዋይነት በማህበረሰብ ሚዛን ላይ ሲሆን ስነ-ምግባር/ግብረ-ገብነት ከአስተዋይነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ስነ-ምግባር/ግብረ-ገብነት ከጋራ ግቦቻችን እንድንደርስ ለማስቻል የተቀመጡ ደንቦች ወይም የደነቦች ስብስብ ነው፡፡

ግብረ-ገብ ትምህርት ለሰው ልጅ ህልውና እና የኑሮ ለውጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ነፃ ህዝብ እና የሰለጠነ ህዝብ ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ መልኩ የሞራል ግዴታን አጠናክረን መያዝ አለብን፡፡ ግብረ-ገብነት መልካም የሆነ ኑሮን ማግኘት እና መኖር ነው፡፡በእርግጠኝነት እስከ አሁንም ድረስ ሰዎች የግብረ ገብ መርሆች ወይም ህጎች ይኖሯቸዋል፡ ፡ ነገር ግን እነዚህን መርሆች እና ህጎች ብቻ ሰዎች ለመፈፀም እና ለማክበር ሀላፊነትን ካልወሰዱ በስተቀር ለግብረ-ገብነት ማረጋገጫ አይሆኑም፡፡ አዎ የግብረ-ገብ እሴቶች በሰዎች የእለት ከእለት ኑሮ ጋር በጥልቀት እየተተገበሩ ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህም አብሮ ለመኖር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ግብረ-ገባዊ እሴቶች የሰው ልጅ በሰዎች ላይ የሚፈጽመውን መጥፎ ተግባራት ለማስቆም በሚችሉበት ደረጃ አላደጉም፡፡ ስለሆነም የግብረ-ገብ ትምህርት ከዚህ በፊት ከነበረው ሁኔታ በበለጠ በአሁኑ ጊዜ በእጂጉ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ግብረ-ገባዊ እሴቶችን እና መርሆችን ማስረጽ ከቻልን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶችን፣ መጥፎ ተግባራትን እንዲሁም የሰው ልጆችን ሰቆቃ ማቅለል እንችላለን፡፡

## የግብረ ገብ ትምህርት ማለት

የታማኝነት፣ራስን የመግዛት፣የብርታት፣የኀደኝነት፣የትሁትነት፣ራስንየማክበር፣ ሌሎችን የማክበር እና የመቻቻልን እሴቶች ማስተማር ማለት ነው፡፡ የግብረ-ገብ ትምህርት ማለት ልጆች ለወደፊት ጥሩ ኑሮ እንዲኖሩ፣ ከሌሎች ጋር ሰላማዊ መስተጋብር እንዲኖራቸው፣ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን እሴቶች እንዲያውቁ ማስቻል ነው፡፡ በሌላ አባባል የግብረ-ገብ ትምህርት በግላዊ መሻሻል እና በተማሪዎች ደህንነት ዙሪያ የማይተካ ሚና አለው ማለት ነው፡፡ የግብረ-ገብ ትምህርት የተማሪዎችን ማህበረዊነት እና ግብረ-ገባዊነትን እንዲሻሻል የሚያስችል ነው፡፡ ስለዚህም ግብረ-ገባዊ እድገት በቀላል ሂደት የሚፈጠር ህገ-ደንብ እና እሴት ሳይሆን የአስተሳሰባዊ ውቅር የለውጥ ሂደት ነው፡፡ ይህም በአስተሳሰባዊ እድገት ለውጥ እና የማህበራዊ ከባቢን ምቹነትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ግልፅ ለማድረግ የአስተሳሰባዊ መዋቅር ለውጥ በጥልቀት የማሰብ፣ ግብረ-ገባዊ ውሳኔ የመስጠት እና ግብረ-ገባዊ ምክንያታዊነትን የመሳሰሉ የተማሪዎችን አስተሳሰባዊ ክህሎቶችን ያሳድጋል፡፡ እንዲሁም ርህራሄ፣ቅንነት፣ መልካምነት፣ የኃላፊነት ስሜት፣ ታማኝነት፣

ፍትሃዊነት፣ ሌሎችን ማክበር እና የመሳሰሉት የተማሪዎችን ስሜታዊ ምክንያቶችን እንዲዳብሩ ያስችላል፡ ፡ በአጠቃላይ የግብረ-ገብ ትምህርት ተማሪዎች በራሳቸው ግብረ-ገባዊ ብቸታዎችን ለማጥራት እና ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን ለመፍታት ያስችላቸዋል፡፡ በድምሩ ግብረ-ገባዊ ትምህርት ለማህበረሰባዊ ጥራት ብዙ አበርክቶ አለው፡፡

## ምዕራፍ አንድ

# ሰብዓዊነትን ማክበር

ምዕራፍ አንድ: ሰብአዊነትን ማክበር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች : ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ :

- የሰብዓዊነትን ትርጉም ታብራራላችሁ፣
- መሰረታዊ የሰብዓዊነት መገለጫዎችን ታብራራላችሁ፣
- ለሰብዓዊነት ክብር ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ፣
- መሰረታዊ የሰብዓዊነትን መገለጫዎች ትገልፃላችሁ፤ በተጨማሪም
- የሰብዓዊነት ክብር አለመኖርን አሉታዊ ውጤት ትለያላችሁ፡፡

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ተማሪዎች ከሰብዓዊነት እና ከሰብዓዊነት ክብር ጋር የሚትተዋወቁበት ነው፡፡እንዲሁም ስለ ሰብዓዊ ክብር ጠቀሜታ ግንዛቤ የሚትጨብጡበት ነው፡፡ ፍቅር፣ ርህራሄ፣ በጎ-አድራጊነት፣ በጎ ፈቃደኝነት፣ ትህትና፣ ወንድማማችነት፣ ታጋሽነት፣ ሰላም፣ መከባበር እና ፍትሃዊነትን የመሳሰሉ መሰረታዊ የሰብዓዊነት መገለጫዎችን በሰፊው የሚያብራራ ነው፡፡

## 1.1 ሰብአዊነት

የሰብአዊነት ፅንስ ሀሳብን መተርጎም ቀላል አይደለም ምክንያቱም በአንድ በኩል የሰው ተፈጥሮን በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ባህሪን ስለሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁለት የተለያዩ የሰብአዊነትን ፅንሰ ሃሳቦች እንወያይባቸው፡፡

### ሀ. የሰው ዘር

የማነቃቂያ ጥያቄ

* የሚከተሉትን ስዕሎች በመመልከት የሰው ልጅ የሆነውን ለዩ




ምስል.1.1. እንሰሳ፤የሰው ልጅ፤እና እቃ

**ተግባር 1.1**

1. የሚከተሉትን ቃላት ወይም ሀረጎች በመጠቀም ክፍት ቦታዎቹን ሙሉ፡፡

ሀ. ምስል ሀ -------------------- ያሳያል፡፡ — እንስሳ
ለ. ምስል ለ -------------------- ያሳያል፡፡ — የሰው ልጅ
ሐ. ምስል ሐ --------------------ያሳያል፡፡ — እቃ

2. በቡድን በመደራጀት ከላይ በቀረቡት እንስሳት ወይም እቃዎች እና በሰው ልጅ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ተወያዩ፤
3. የቡድናችሁን የውይይት ውጤት ለሌሎች አጋሩ፡፡

ሰብአዊነት ማለት የሰው ዘር ወይም የሰው ልጅ ማለት ነው፡፡ የሰው ልጆች የተለያ ችሎታዎች ስላለቸው ልዩ ፍጡር ናቸው፡፡

**ለምሳሌ፡** የሰው ልጆች ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማሰብ የሚችሉ፤ራሳቸውን ችለው ውሳኔ የሚወስኑ፤ነፃነት እና ክብር ያላቸውና ለሌሎች ክብር የሚሰጡ ናቸው፡፡

የሰው ልጆች በዘር ፣ በቁመት ፣ በፆታ ፣ በቋንቋ ፣ ወ.ዘ.ተ የተለያዩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም በሰብአዊነታቸው እኩል ናቸው፡፡ በመሆኑም እናንተ ጓደኞቻችሁን በአስተዳደጋቸው፤በኢኮኖሚ ሁኔታ ወይም በሌላ መስፈርቶች ልዩነት የተነሳ አድልዎ ማድረግ የለባችሁም፡፡ ስለዚህ ሰብአዊነት ስለ ሁሉም የሰው ልጆች እኩልነት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

## ለ. የመልካምነት ባህርይ

ከዚህ ስዕል ምን ትማራላችሁ?



ምስል. 1.2. በሰው ልጆች መካከል ያለ መተባበር

**ተግባር 1.2**

**አራት ተማሪዎችን ያቀፈ ቡድን አቋቁሙ እና ከላይ ያለውን ስዕል በተግባር አሳዩ፡፡ ከዚያም የሚከተሉትን ሃሳቦች ጮክ ብላችሁ ተናገሩ፡፡**

“እኛ የሰው ልጆች ነን፡፡ ሰብአዊነት መልካምነት ነው፡፡ ሰብአዊነት መተባበር ነው፡፡እኔ የእናንተ ነኝ በሚያስፈልጋቹህ ጊዜ ሁሉ እደግፋችኃለሁ፡”

1.እናንተስ ?

2. ከጓደኞቻችሁ ጋር ስለ መተባበር ያላችሁን ሀሳብ አካፍሉ፡፡

ሁለተኛውን የሰብአዊነት ፅንስ ሀሳብ ከላይ ተማሪዎቹ ካሳዩት ተግባር መማር እንችላለን፡፡ ሰብአዊነት ማለት ከልብ የመነጨ መልካምነት፤ሰዎች

ድጋፍ ሲያስፈልጋቸው ያለ አድልዎ ድጋፍ መስጠትን፤ ሰዎች እርስ በርስ እንዲግባቡ እና ወዳጅነት እንዲመሰርቱ የሚያስችል ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰብአዊነት በውስጡ ሰላምን፤መተባበርን ከማካተቱም በላይ በሰው ልጆች እና በተማሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲዳብር ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች መልካም ባህሪ በማጎልበት በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ለተቸገሩ ደራሽ መሆን ያስፈልጋል፡፡

## 1.2 ሰብአዊ ክብር

### የማነቃቂያ ጥያቄ



* ተማሪዎች ከሰው ልጅ ተነጥሎ መኖር የሚችል አንድ ነገር ልትናገሩ ትችላላቹሁ?

በሚከተሉት ስዕሎች መካከል ያለውን ልዩነት ለይታችሁ አውጡ፡፡




ምስል. 1.3. የተለያዩ የደረጃ አሰጣጥ መንገዶች

**ተግባር 1.3**

**በሁለቱ ስዕሎች መካከል ያለውን ልዩነት ጥቀሱ?**

በቀላል አገላለጽ "ሰብአዊ ክብር" ማለት "የሰው ዋጋ" ማለት ነው፡፡ ሰብዓዊ ክብር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከሰው ልጅነት ፈጽሞ የማይለይ ከመሆኑም በላይ የሰው ልጅ ዋጋ አለው ከሚለው ሀሳብ ጋር በጣም ይያያዛል ፡፡ ሁሉም ሰው ነጻ ሆኖ በክብርና በመብት እኩል ሆኖ ይወለዳል፡፡ የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው ሰብዓዊ ክብር ያላቸው ከመሆኑም በላይ እርስ በርሳቸው በወንድማማችነት መንፈስ መተጋገዝ አለባቸው፡፡ ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ በተፈጥሮ ዋጋ አላቸው፡፡

ተግባር 1.4.

ሰዎች ክብራቸውን ሊያጡ ይችላሉ?

| ክርክር | |
|---|---|
| ቡድን ሀ (አዎ) | ቡድን ለ(አይደለም) |
| ሰዎች ክብራቸውን እንዴት እንደሚያጡ ጥቀሱ? | ይህ ያልሆነበትን ምክንያት አብራሩ. |
| | |
| | |
| | |

ሰብዓዊ ክብርን ማጣት፤ ምንም እንኳን ሰብአዊነት ተወራራሽ ቢሆንም የሰው ልጅ ሰብአዊ ክብሩን የሚያጣበት አጋጣሚ አለ፡፡አንደኛ ሰዎች ለራሳቸው ጥሩ ግምት ባለመስጠታቸው ክብራቸውን ሊያጡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ብዙውን ጊዜ ሰዎች በሰብአዊነታቸው ሳይኮሩ ሲቀሩ ክብራቸውን ያጣሉ ፡፡ ሁለተኛ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት በመሥራታቸው ክብራቸውን ያጣሉ፡፡ በተጨማሪም ብዙውን ጊዜ ሰዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት የሌላቸው ነገሮችን ሲያደርጉ ክብራቸውን ያጣሉ ፡፡ ለምሳሌ ማጭበርበር፣ ታማኝ አለመሆን፣ መዋሸት፣ ሙስና፣ መግደል፣ ሀሳተኝነት፣ ወዘተ. ሰዎች ክብራቸውን እንዲያጡ የሚያደርጉ መጥፎ ባህሪያት ናቸው ፡፡

ተግባራት 1.5

1. በእናንተ ማኅበረሰብ ውስጥ ትልቅ ክብር ያላቸው ሰዎችን ጥቀሱ፡፡ ያበረከቱት አስተዋፅኦስ ምንድን ነው?
2. በመጥፎ ባህሪያችሁ ምክንያት ሰብዓዊ ክብራችሁን ብታጡ ምን ይሰማችኋል?

## 1.2.1 ሰበአዊነትን ማክበር እና ያለው ጠቀሜታ

ማነቃቅያ ጥያቄ



*በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ክብር የሚሰጡበትን ምክንያት ተናገሩ፡፡

ለሰዎች ክብር መስጠት የተለመደ የኢትጵያውያን ባህል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ አንዳቸው ለሌላቸው በመከበበር ይኖራሉ፡፡ ሰዎች የሌሎችን ሰብአዊ ክብር የሚያከብሩ ከሆነ የእነሱም ሰብአዊ ክብር በሌሎች ዘንድ ይከበራል፡፡

የሰብአዊ ክብር አስፈላጊነትን የሚያሳዩ ምሳሌዎች ከታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ያጠቃልላሉ፡፡

- ሰብአዊ ክብር ለሰብአዊ መብት ዋና መሰረት ነው፡፡ስለዚህም ሰብአዊ መብት ከሰብአዊ ክብር የማይነጣጠል ሓሳብ ነው፡፡
- ሰብአዊ ክብር ለሰብአዊ እርዳታ መሰረት ነው፡፡ ጓደኞቻችሁ የየናንተን እርዳታ በፈለጉ ጊዜ ሁሉ መርዳት ይኖርባችኋ ል፡፡
- ይህን ማድረግ የሚቻልው የገንዘብ ፤ የአልባሳት፤የምግብ ፤ የመጠጥ ውሃ ወዘተ በመስጠት ነው፡፡
- ሰብአዊ ክብር ሰብአዊ መብትን የሚመለከቱ ሕጎችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡የሰብአዊ መብት ሕጎች “ሁሉም የሰው ልጆች ነጻ፤ በክብርና በመብት እኩል የሚወለዱ ናቸው” የሚል ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

ተግባር 1.6

1.በማህበረሰባችሁ ውስጥ ለሰው ክብር መስጠት ለምን እንደሚያስፈልግ ተወያዩ፤

2. ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሰብዓዊ ክብርን በማክበር ረገድ ያላችሁን ተሞክሮ አካፍሉ፡፡

## 1.3 የሰብአዊነት መሰረታዊ መገለጫዎች

### 1.3.1 ፍቅር

የማነቃቂያ ጥያቄ



* የበለጠ የምትወዱት ማንን ነው ?

ውይይት

ሃና፣ ሱልጣን እና ገለቴ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ማን ማንን የበለጠ እንደሚወድ እርስ በርሳቸው መተማመን ስላልቻሉ መፍትሔ ለማግኘት ወደ አስተማሪያቸው ሄዱ፡፡ ሃና እንዲህ ትላለች ፦ “አባቴ ሁልጊዜ ቸኮሌት ስለሚያመጣልኝ እወደዋለሁ፡፡” ሱልጣን እናቱ ብስክሌት ስለገዛችለት እንደሚወዳት ይናግራል ፡፡

የገለቴ አቋም ግን ከሁለቱ የክፍል ጓደኞቿ በጣም የተለየ ነው፡፡ ቤተሰቦቿን፣ ጎረቤቶቿንና ጓደኞቿን በሙሉ በጣም ትወዳለች፡፡በመጨረሻም አስተማሪያቸው የሁሉንም ምላሽ አድንቆ ሁሉንም ሰው መውደድ እንዳለባቸው መከራቸው፡፡ ስለዚህ ፍቅር ሁልጊዜ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ ነገር አይደለም፡፡

ተግባር 1.7.

1. ከሶስቱ ተማሪዎች የማን አቋም ስሜት ይሰጣችኋል? ለምን?
2. የገሊቴ አቋም ከሌሎች ጓደኞቿ ለምን ተለየ?

“ፍቅር”ለአንድ ሰው ወይም ነገር ያለን ጥልቅ የሆነ የወዳጅነት እና የመተሳሰብ ስሜት ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ፍቅር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከአንድ ሰው ጋር ስሜታዊ ቅርርብ መመሥረትን ይጨምራል፡፡ "ፍቅር" መተሳሰር ፣ ቁርጠኝነት ፣ የጠበቀ ወዳጅነት እና ጥልቅ ስሜትን ጽንሰ ሀሳቦችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ፍቅር ካልሰመረ ጥልቅ ሓዘን ሊያስከትል ይችላላ፡፡

ከታች ያሉትን ስዕሎች ተመልከቱ እና ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ፡፡



ምስል. 1.4. ሀ. ማኩረፍ



ምስል. 1.4. ለ. ፍቅር በጓደኛሞች መሃል

ተግባር 1.8

1.ከላይ ከተሰጡት ስዕሎች ምን ተማራችሁ?
2.የደስታ ምንጭ ምንድን ነው?
3.በቤታችሁ ውስጥ ያላችሁን ልምድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

» ሽየተለያዩ የፍቅር ዓይነቶች አሉ፡፡

1.የቤተሰብ ፍቅር: አንድ ሰው ቤተሰቧን/ቡን ልክ እንደራሷ/ሱ መውደድ አለባት/ባት፡፡ ቤተሰባችሁ ምን ያህል ደስተኛ እና ሰው ወዳድ እንደሆኑ አስቡ፡፡



ምስል1.5፡ የቤተሰብ ፍቅር

2.የጓደኛሞች ፍቅር: በምትኖሩበት አከባቢ እና በትምህርት ቤቱ ውስጥ በርካታ ጓደኞች ይኖሯችኋል። ስለዚህ ስትማሩ፣ ስትጫወቱ፣ ስትበሉ እና አብራችሁ ስራ ስትሠሩ እርስ በርሳችሁ መዋደድ አለባችሁ።



ምስል. 1.6. የጓደኛሞች ፍቅር

3.“የሀገር ፍቅር” የሀገር ወዳድ ሰዎች ባህሪ ነው። ሀገር ወዳድ ሰዎች ሀገራቸውን ስለሚወዱ ለሀገራቸው መስዋዕት ይሆናሉ። ስለዚህ ሀገራችሁን ሁሌም መውደድ አለባችሁ።



ምስል. 1.7. የሀገር ፍቅር

ተግባር 1.9

1. እርስ በርስ ስለ መዋደድ ምን ታስባላችሁ?
2. አብልጣችሁ የምትወዱት ምንድን ነው?

## 1.3.2 ርህራሄ እና ጨዋነት

የማነቃቂያ ጥያቄ



* ሩህሩህ የሆነ ሰው ልትጠቅሱ ትችላላችሁ?

ሄዋን ፣ ሲፈን ፣ ጎይቶምና ጫቄቦ የክፍል ጓደኛሞች ናቸው። ጎይቶም በመኪና አደጋ ምክንያት አንድ እግሩን ያጣ የአካል ጉዳተኛ ነው። በሚያሳዝን ሁኔታ ሄዋን በትምህርት ቤቷ የአትክልት ስፍራ ሆና ከአንድ ወር በፊት የሞቱት

እናቷን በማስታወስ እያለቀሰች ሳለች የቅርብ ጓደኛዋ ሲፈን አገኘቻትና እሷም ተመሳሳይ ስሜት ተሰማት ። ይሁን እንጂ ሲፈን ስሜቷን ከመግለጽ በስተቀር ለጓደኛዋ ምንም ነገር አላደረገችላትም። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ጫቂቦ ርቦት ብቻውን ተቀምጦ ሳለ ጎይቶም ደረሰለትና ጫቂቦን ወደ ትምህርት ቤቱ ሻይ ቡና ክበብ ወስዶ ጋበዘው ። በተጨማሪም ጎይቶም ጫቂቦ ምን እንደደረሰበት ለመምህሮቹ ነግሮ እነሰ የደረሰበትን ችግር አይተው ችግሩን እንዲፈቱለት አደረገ።

> **ተግባር 1.10**
>
> 1.ሲፈንን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?
>
> 2.ጫቂቦን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ርህራሄ እና ሃዘኔታ የሰው ልጅ መሠረታዊ የሰብአዊነት መገለጫዎች ሲሆኑ በተለያዩ መንገዶችም ሊታዩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ሁለቱም በተለዋዋጭነት በሰፋት ጥቅም ላይ ይውላሉ። በዚህም መሰረት ርህራሄ እና ሃዘኔታ እንደ ልግስና ደግነት እና የሰውን ችግር እንደ ራስ ማየት የሚሉትን መሰረታዊ ባህርያት ይጋራሉ። እስኪ እያንዳንዱን ጽንሰ-ሀሳብ በተናጠል እንወያይባቸው።

**ርህራሄ:** ማለት የሌሎችን ስቃይ ለማቅለል ፍላጎት ያለው ጥልቅ ግንዛቤ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ርህራሄ የመርዳት ፍላጎትን ያመለክታል እንጂ በተግባር ላይ ማዋልን አያመለክትም። ርህራሄ ጥልቅ ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ለሌሎች የበለጠ መጎዳትን ያሳያል። በመሆኑም ርኅራኄ በሰዎችና መካከል አብሮነትና ቁርጠኝነት ይገነባል



ምስል. 1.8. ርህራሄ በጓደኞሞች መሃል

**ህዘኔታ**: የሌሎች ሰዎችን ስሜት መረዳት ማለት ሲሆን በውስጡ ድርጊት እና ድጋፍን ያካትታል። ህዘኔታ የሌላውን ሰው ስሜት የመለየትና የመረዳት ችሎታ ሆኖ በችግር ላይ ላሉ መፍትሄ መፈለግንም ይጨምራል።ስለዚህ ተማሪዎች የርህራሄ እና የህዘኔታ ልምድ በየዕለት ተዕለት ተግባራቸው እንዲያዳብሩ ይጠበቃል። በተጨማሪም ተማሪዎች የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸውን ሰዎች መርዳት አለባቸው።



ምስል. 1.9. ህዘኔታ በጓደኞች መካከል

**ተግባር 1.11**

በርህራሄ እና በህዘኔታ መካከል ያለውን ልዩነት ተወያዩበት።
ከላይ ከተሰጡት ሁለት ስዕሎች ምን ተማራላችሁ?

## 1.3.3 በጎ አድራጊነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

በጎ አድራጊ የሆነ ሰው ወይም ድርጅት ልትጠቅሱ ትችላላችሁ?



ምስል 1.10 ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና የተቸገሩ ሰዎችን ሲረዱ

ተግባር 1.12

1. ስለ አበበች ጎበና ምን ታውቃላችሁ?
2. ለአንድ ሰው ያለ ክፍያ ወይም በነፃ የሆነ ነገር መስጠት ምን ማለት ነው?

በጎ አድራጎት ከሁሉ የላቀ የፍቅር መገለጫ ነው፡፡ በጎ አድራጎት ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ አንዱ ለሌላው የሚሰጠውን ፍቅር ያመለክታል፡፡ በጎ አድራጎት በነፃ ሰዎችን መርዳት ነው፡፡ በጎ አድራጎት በሌላ በኩል ለታመሙ፣ ለድሆች እና አቅመ ደካሞች ገንዘብ በማሰባሰብ እርዳታ የማድረግ ተግባር ነው፡፡ በጎ አድራጎት በጣም አስፈላጊ ከመሆኑም የተነሳ ለህዝብ ጥቅም እና ዕረፍት የሚሰጥ ሰናይ ተግባር ነው፡፡እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች መካከል የተፈጥሮ አደጋ የደረሰባቸው፣በጦርነት፣ በረሃብ፣ በበሽታ፣ በድህነት የተጎዱ እንዲሁም ምግብ፣ መጠለያና የሕክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወላጅ አልባ ልጆች ይገኙበታል፡፡

ተግባር 1.13

1. ስለ በጎ አድራጎት ምን ታስባላችሁ?
2. በአከባቢያችሁ ላሉ ችግረኞች ምን አስተዋፅኦ ታበረክታላችሁ?

## 1.3.4 በጎ ፈቃደኝነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**



በአከባቢያችሁ በበጎ ፈቃደኝነት የሚደረጉ ተግባራትን ልትጠቅሱ ትችላላችሁ? ከታች ያለውን ስዕል ተመልከቱና ተማሪዎቹ ምን እየሰሩ እንደሆነ ተናገሩ፡፡



ምስል 1.11. ተማሪዎች በበጎ ፈቃድ ተግባር ላይ

ተግባር 1.14

በሥዕሉ ላይ ስለተመለከታችሁት የተማሪዎቹ ተግባር ምን ትላላችሁ?
በእንደዚህ አይነት ተግባራት በፍቃደኝነት ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ?

በጎ ፈቃደኝነት ማለት ለሌሎች ሰዎች ጥቅም ሲባል ጊዜን እና ክህሎትን የመስጠት ልምድ ሲሆን ለበጎ ፈቃደኛው የገንዘብ ጥቅም አያስገኝም፡፡ በጎ ፈቃደኝነት ለግለሰብም ሆነ ለቡድን ያለ ምንም ክፍያ በነፃ ጊዜን እና ጉልበትን ለማህበራዊ አገልግሎት ማዋል ነው፡፡ በጎ ፈቃደኛ በአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴ፣ በመልሶ ማልማት ጥረቶች፣ እንዲሁም ሌሎችን ስለ አካባቢ ጥበቃ በማስተማር ተግባር ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በጎ ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ወይም በደም ልገሳ ተግባር ላይ በፈቃደኝነት በንቃት ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡

ተግባር 1.15

የትምህርት ቤት ግቢያችሁን በማጽዳት በጎ ፈቃደኝነትን በተግባር አሳዩ፡፡

## 1.3.5. ጨዋነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* ከሰዎች ጋር ስትገናኙ ትኅትናችሁን እንዴት ታሳያለችሁ?



ምስል.1. 12. ጨዋነት ወይም ትህትና

ተግባር 1.16

ተማሪዎች ከላይ ካለው ስዕል ምን ትማራላችሁ?

“ጨዋነት” ማለት ለሌሎች ትህትና ማሳየት ማለት ነው ። ጨዋነት የአንድን ሰው ማንነት፣ ፍላጎትና እምነት ሳይነኩ መንከባከብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። እንደ ትሕትና እና መልካም ስነ- ምግባር ያሉ የሰዎች ባህርያት የጨዋነት ምሳሌዎች ናቸው። ጨዋነት መከባበርን ፣ከእንግዶች ጋር ያለን ግንኙነት እና ራሰን መግዛትን ያጠቃልላል።

ጨዋነት የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት:

- የሌሎችን መብት ማክበር
- ለሌሎች ሰዎች ክብር እውቅና መስጠት እና ማክበር
- በሁሉም ሰዎች ተፈጥሮአዊ መልካምነት ማመን

ምሳሌ

በተለያዩ ቦታዎች ጨዋነትን ማሳየት እንችላለን ። አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ወይም በሌሎች መስኮች እግር ኳስ ይጫወታሉ። አንደኛው ተጫዋች ሜዳ ላይ ጉዳት ሲደርስበት ሌላኛው ደግሞ እንዲረዳው ይጠበቃል። በተለያዩ ቦታዎች ለእኩዮቻችን ሃዘኔታ እንዳለን ማሳየት ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ ይህ ነው ።



ምስል.1.13. ጨዋነት በእግርኳስ ሜዳ

ተግባር 1.17

1. ከላይ ካለው ስዕል ምን ትማራላችሁ?

ጨዋነትን በተመለከተ ያላችሁን ተሞክሮ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

## 1.3.6 ወንድማማችነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ?**

የቅርብ የትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁንና ጎረቤቶቻችሁን ምን በማለት ትጠራላችሁ?

ወንድማማችነት በቡድን ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከል የሚኖር የወዳጅነት ስሜት በመሆኑም የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ስሜትን ይቀሰቅሣል :: ይህም በቀሪው የህይወት ዘመናቸው በቡድን አባላት መካከል የጋራ ግብ እና ምኞት የመመሥረት ዘዴ ነው:: በተጨማሪም ወንድማማችነት የሚያመለክተው በአንድ ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሠሩ ፣ ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ወይም በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሰዎችን ያመለክታል::



ምስል. 1.14. ወንድማማችነት: የወንድማማችነት እና የእህታማማችነት ስሜት

**ተግባር 1.18**

1.ከላይ ካለው ስዕል ምን ትማራላችሁ?

2.እንደ እህት እና ወንድም የምትቀራረቡበት የተማሪዎች ቡድን አላችሁ?

3.ወንድማማችነት/ እህትማማችነት ስላለው ጠቀሜታ ምን ታስባላችሁ?

በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ከላይ በተጠቀሰው የወንድማማችነት/ እህትማማችነት ፍቺ ላይ ተመሥርተው የወንድማማችነት/እህትማማችነት ስሜት ማዳበር ይችላሉ:: በወንድማማችነት/እህትማማችነት መንፈስ ወዳጅነታቸውን ማጠናከር አለባቸው:: አንደኛው ሌላውን እንደ ራሱ ወንድም ወይም እህት አድርጎ መመልከት ይኖርበታል:: የወንድማማችነት/እህትማማችነት አላማ አባላቱ አብረው እንዲማሩና እንዲያድጉ ለማስቻል ነው:: ይህም ዕድሜ ልካቸውን የሚዘልቅ ጠንካራ ወዳጅነት ለመመሥረት ያስችላቸዋል ::

## 1.3.7 ታጋሽነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

አስተማሪዎቻችሁ ወደ ክፍል እስኪገቡ ድረስ ምን ታደርጋላችሁ?

## ጭውውት

- ቃልኪዳን: ቤተሰቦችህ ቃል የገቡልህን ነገር ለመግዛት ሲዘገዩ ምን ይሰማሃል?
- ከድር: ቃለ የገቡትን ነገር እስኪፈጽሙ ድረስ ሁልጊዜ ማታ ማታ እረብሻቸዋለሁ::
- ቃልኪዳን: እንዴ ይህ ባህሪ በጣም መጥፎ ነው:: ታጋሽ መሆን አለብህ::
- ከድር: ይቅርታ "ታጋሽ" ስትይ ምን ማለትሽ ነው?
- ቃልኪዳን:እስኪገዙልህ ድረስ ሳታስቸግር በትዕግስት መጠበቅ ማለት ነው::
- ከድር: አመሰግናለሁ ቃልኪዳን እኔም አንቺ እንዳደረግሽው አደርጋለው::

> ተግባር 1.19
>
> 1.ከቃልኪዳንን እና ከከድር ጭውውት ምን ተማራችሁ?
>
> 2.ልምዳችሁን ለቡድን አባላቶቻችሁ አካፍሉ::

ለምሳሌ ያህል፣ አስተማሪዎቻችሁ ወደ ክፍል ዘግይተው ቢመጡ በትዕግሥት መጠበቅ ይኖርባችኋል:: ቤተሰቦቻችሁ ልብስ ለመግዛት ሲዘገዩ ችግራቸውን ተረድታችሁ እስኪገዙላችሁ ድረስ በትዕግሥት መጠበቅ አለባችሁ::



ምስል. 1.15. ታጋሽ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ

ታጋሽነት ያለምንም ቅሬታ በትዕግስትና፣ በፈቃደኝነት የመጠበቅ ችሎታ ነው:: ታጋሽነት ችግሮችን ፣ መጥፎ ዕድልንና መከራን በሰላማዊ መንገድ ለመቋቋም ወይም ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው :: በመሆኑም ሌሎች ጨዋ እንዲሆኑና አንድ ነገር እስኪያገኙ ድረስ በትዕግስት እንዲጠብቁ ማስተማርን ያካትታል::

### 1.3.8 ሰላም

**የማነቃቂያ ጥያቄ**



ሰዎችን ስታገኙ እንዴት ነው ሰላምታ የምትሰጡት?

ሰዎች የማይመች ሁኔታ ቢያጋጥማቸውም እንኳ እርስ በርስ ሰላምታ

ይለዋወጣሉ:: ሰላምታ ለሰላምና ለመልካም ግንኙነት አስተዋፅኦ አለው:: ሰላም ለማውራት፣ ሰላምታ ለመለዋወጥ እና እርስ በርስ ለመጫወት ያስፈልጋል::




ምስል.1.16. ሰላምታ ተላላፊ ቫይረሶች ባሉበት እና በጤናማ ሁኔታ

**ተግባር 1.20**

1.በ ኮቪድ 19 ጊዜ ለሰዎች ሰላምታ የምትሰጡበትን መንገድ አሳዩ::

2. በሰላምና በሰላምታ መካከል ስላለው ግንኙነት ተወያዩ::

ሰላም በተማሪዎች እና በሰዎች መካከል ያለ መልካም/ጤናማ ግንኙነት ነው:: ሰዎች ይበልጥ ተባብረው እንዲሰሩ ያስችላቸዋል:: ሰላም የህዝብ አንድነት ዋና መሰረት ነው:: በተጨማሪም ሰላም ለቤተሰብ ፣ ለትምህርት፣ለጎረቤት፣እና ለሃገር ፍቅር መሰረት ነው:: በጓደኞች መካከል ሰላም አለመኖሩን የሚያሳዩ የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ ::



ምስል. 1.17. ግጭት በጓደኞሞች መካከል

**ተግባር 1.21**

1.ከላይ ካለው ስዕል ምን ትማራላችሁ?

2. እርስ በርስ መጣላት ያለውን መጥፎ ጎን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

የሰላም አለመኖር ወደ ግጭት ያመራል። ግጭት መጥፎ ድርጊት ነው ። እርስ በርስ ወደ መጣላት የሚያመራ ሲሆን ይህም ሁለቱንም ጓደኞች ይጎዳል። ስትጣሉ ጥርሶቻችሁ፣ ዓይኖቻችሁን ወይም ሌላ የሰውነታችሁን ክፍል ልታጡ ትችላላችሁ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሰብአዊነት የሰው ዘርን የመልካምነት እና የደግነት ባሕርይ ያመለክታል። ሰብአዊነት የሁሉንም ሰዎች እኩልነት ያለአድሎ መከበርን ያረጋግጣል። ስለዚህ ሁላችሁም በመጀመሪያ ሰብአዊነትን ማክበር ይጠበቅባችኋል። ሰብዓዊ ክብር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከሰው ልጅነት ፈጽሞ የማይለይ ከመሆኑም በላይ የሰው ልጅ ዋጋ አለው ከሚለው ሀሳብ ጋር በጣም ይያያዛል። ሰብዓዊ ክብር አንዳንድ ጊዜ በግለሰብ ባሕርይና ድርጊት ላይ ተመሥርቶ ክብር ሊያሳጣ ይችላል። ሰብአዊ ክብርን ማክበር ለሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ ለሰብአዊ ዕርዳታና ለሰብአዊ መብት ሕጎች መሰረት በመሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው። ሰብአዊነት ፍቅርን፣ ርኅራኄን፣ በጎ አድራጎትን፣ በጎ ፈቃደኝነትን፣ ጨዋነትን፣ ወንድማማችነትን/ እህትማማችነትን፣ ታጋሽነትን፣ ሰላምን፣ መከባበርንና ፍትሃዊነትን የሚያጠቃልሉ መሰረታዊ መገለጫዎች አሉት።

**ቁልፍ ቃላት**

መልካምነት: የደግነት ባህርይ።

ክብር: ክብር ወይም አክብሮት የሚገባው።

ሀዘኔታ: የሌሎች ስሜት የመጋራት ችሎታ ።

ፍትሃዊነት: መደረግ ያለበትን ነገር በተመለከተ ጥሩ ውሳኔ የማድረግ ችሎታ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች

**ክፍል አንድ: ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ። ።**

1. ሰብአዊነት የሁሉንም ሰዎች እኩልነት ያረጋግጣል።
2. ሰብዓዊ ክብርን ማክበር የአንዳንድ ሰዎች ኃላፊነት ነው።
3. ታጋሽነት ያለምንም ቅሬታ በትዕግስት ወይም በእርጋታ የመጠበቅ ችሎታ ነው።
4. "ጨዋነት" ማለት ለሌሎች ትህትና ማሳየት ነው።
5. በጎ ፍቃደኝነት ለራስ ጥቅም ጊዜንና ክህሎትን የማዋል ተግባር ነው።

**ክፍል ሁለት፡ በ " ሀ " ምድብ የተሰጡትን ማብራሪያዎች በተመሳሳይ ከ "ለ" ምድብ ከተሰጡት ጽንሰ ሀሳቦች ጋር አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.ጥልቅ የሆነ የወዳጅነት ስሜት | ሀ. ርህራሄ |
| 2.የፍቅር ጥግ | ለ. ፍቅር |
| 3.ለሌሎች ትህትና ማሳየት | ሐ. በጎ አድራጊነት |
| 4.ለሌሎች ክብር እና ዋጋ የመስጠት ችሎታ | መ. ጨዋነት |
| 5.የሌሎችን ስቃይ መገንዘብ እና ዕረፍት የመስጠት ችሎታ | ሠ.አክሮት |

**ክፍለ ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ መልስ ስጡ።**

1. ሰብአዊነትን ክብርን ለማክበር አስፈላጊ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ሰብአዊ መብትን ማክበር።

   ለ. ሰብአዊ እርዳታ ማድረግ።

   ሐ. የሰብአዊ ድንጋጌዎች መጠበቅ።

   መ. ሰብአዊ መብት ጥሰትን መፈጸም ።

2. ከሚከተሉት ውስጥ ግለሰቦች ለማህበረሰብ አገልግሎት ያለ ክፍያ ጊዜና ጉልበታቸውን በነጻ የሚሰጡበት ድርጊት የትኛው ነው?

   ሀ. ጨዋነት ሐ. በጎ ፈቃደኝነት

   ለ. ወንድማማችነት መ. ታጋሽነት

3. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃዎች ላይ በመመስረት የሰዎችን ተገቢና ምክንያታዊ አያያዝን የሚያመለክተው የትኛው?

   ሀ. ሰላም ሐ. ሀዘኔታ

   ለ. ፍትሃዊነት መ. በጎ አድራጎት

**ክፍል አራት: እነዚህን ተግባራት ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በቤት ውስጥ ስሯቸው፡፡**

1. ሰብአዊነትን የማክበር አስፈላጊነት ዘርዝሩ፡፡
2. በማህበረሳባችሁ ውስጥ ሰብአዊ ክብርን ሊያሳጡ የሚችሉ ተግባራትን ጥቀሱ፡፡
3. ቤተሰቦቻችሁን ታከብራላችሁ? በዚህ ረገድ በቤታችሁ ምን ዓይነት ተግባር ታከናውናላችሁ?
4. በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ በፈቃደኝነት በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ትሳተፋላችሁ? ምሳሌዎችን ጥቀሱ?

## ምዕራፍ ሁለት

# ሌሎችን ማክበር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች: ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኃላ:

- ሌሎችን ስለማክበር ፅንስ ሀሳብ ታብራራላችሁ፣
- ሌሎችን ማክበር ለምን እንደሚያስፈልግ ትገልፃላችሁ፣
- የሌሎችን አመለካከትና ፍላጎት የማድነቅ ባህሪ ታሳያላችሁ፣
- የሌሎችን ፍላጎት እና አመለካከት ታከብራላችሁ፣
- የተከበረ ሰው ባህርይን ትገልፃላችሁ፤
- ሌሎችን ያለማክበር የሚያስከትለውን ውጤት ትለያላችሁ፡፡

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ሌሎችን ስለማክበር የሚገልፀ ነው፡፡ በተጨማሪም ምዕራፉ የማኅብረሰቡን የተወሰኑ ክፍሎች በመጥቀስ ሌሎችን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ያብራራል፡፡ ከእነዚህም መካከል አረጋዊያንን፣ የሃይማኖት አባቶችን ፣ አስተማሪዎችን ፣ ቤተሰብን ፣ ጎረቤቶችንና የክፍል ጓደኞችን ማክበርን ያካትታል፡፡ ከዚህም በላይ የተከበሩ ሰዎች ባህርይን ይመለከታል፡፡ በመጨረሻም ሌሎችን ያለማክበር የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ይመለከታል፡፡

## 2.1. አክብሮት

የማነቃቂያ ጥያቄ

*ለሌሎች ያላችሁን አክብሮት እንዴት ታሳያላችሁ?

በምዕራፍ አንድ መጨረሻ ላይ ሰብአዊነትን ስለ ማክበር ተምራችኋል ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ሌሎችን ስለማክበር ትማራላችሁ፡፡

ተግባር 1

1.ሰብአዊነትን ስለማክበር የምታስታውሱትን ተናገሩ፡፡

2. ከታች ያለውን ስዕል ተመልከቱ እና ሌሎችን እንዴት እንደምታከብሩ አሳዩ፡፡



ምስል 2.1 ሌሎችን ማክበር

አክብሮት ለአንድ ሰው ከፍ ያለ ግምት የመስጠትና የማክበር ችሎታን ያመለክታል ፡፡ አክብሮት በተግባርም ሆነ በቃላት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡ የሰው ልጆች በማንኛውም ጊዜ በሁሉም ቦታ መከበር አለባቸው፡፡ ስለዚህ ሰዎች እርስ በርሳቸው የመተማመን ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል፡፡ ከዚህም በላይ በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል ፡፡ አክብሮት በተሞክሮ የምትማሩትና የምታዳብሩት ነገር ነው እንጂ፤ በተፈጥሮ የሚገኝ አይደለም፡፡ ሦስት የአክብሮት ዓይነቶች አሉ ፡፡ እነሱም

ሀ. ራስን ማክበር

ለ. ሌሎችን ማክበር እና

ሐ. ሌሎች ሰዎች ለእኛ ያላቸው አክብሮት ናቸው፡፡

የመከባበር መርህ የአንድ ሰው የመከበር ፍላጎት ነው ፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው በሌሎች ዘንድ መከበር ከፈለገ ሌሎችን ማክበር አለበት ማለት ነው ፡፡

ተግባር 2

1. በማህበረሰባችሁ ውስጥ እርስ በርሳችሁ የምትከባበሩበትን መንገድ አሳዩ::.
2. ለቡድናችሁ እና ለመምህራችሁ ስለአክብሮት ያላችሁን ሀሳብ ተናገሩ::

## 2.2. ሌሎችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

* ከሰዎች ጋር ስትገናኙ ምን ታደርጋላችሁ?

ከላይ እንደተማርነው አክብሮት ማለት ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ክብር የምናሳይበት መንገድ ነው :: “ሌላ” የሚለው ቃል ከእናንተ በስተቀር ማንንም ያመለክታል:: ይህ ክፍል ግን በአንዳንድ ማህበራዊ ቡድኖች ላይ ያተኩራል:: ሌሎችን ማክበር የሚጀምረው አንድ ሰው ራሱን ችሎ ፣ ልዩና ነፃ እንደሆነ በመገንዘብ ነው :: አንድን ሰው ማክበር ለራሳችን ክብር እንዲኖረን ያደርጋል ::በተጨማሪም ለሰዎች ሰብዓዊ ክብር ዋጋ መስጠት እና ማክበር ነው:: ከዚህም በላይ በተለያዩ ማህበራዊ ስራ ላይ ያሉ ሰዎችን ማክበር ነው:: የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተመልከቱ:



ምስል.2.2. እርስ በርስ መከባበር

ከላይ በምስሉ ላይ እንዳያችሁት ለሌሎች ያለንን ክብር በተለያየ መንገድ መግለፅ እንችላለን:: ሰላምታ፣ ትህትና፣ መልካምነት ወይም ጨዋነት፣ አመስጋኝነት፣ ታዛዥነት ለሌሎች አክብሮት ለማሳየት የሚረዱን መንገዶች ናቸው::

**ተግባር 3**

1. ከላይ ከተጠቀሱት ድርጊቶች ውስጥ የትኛውን በየቀኑ ትጠቀማላችሁ?
2.ልምዳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡
3.ለሌሎች አክብሮት ስታሳዩዋቸው እንዴት ምላሽ ይሰጣሉ?

## 2.3 ሌሎችን የማክበር አስፈላጊነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

* ሌሎችን የማክብር አስፈላጊነት ምን እንደሆነ ጥቀሱ?

ለሌሎች አክብሮት ማሳየት ሌሎችን የሚያከብሩ ሰዎች ራሳቸውም እንዲከበሩ ይጠቅማቸዋል፡፡ አክብሮት እርስ በርስ ለመቀራረብና ለመከበር ትልቅ ግምት ይሰጣል እናም ደህንነትና ደስታ እንዲሰማን ይረዳናል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ሌሎች እኛን በአክብሮት እንዲመለከቱን እና እንዲይዙን ስለሚረዳ ነው ፡፡ ለሰው ልጆች አክብሮት ማሳየት መሠረታዊ ነገር እንደሆነ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡ በተመሳሳይም ሌሎችን ማክበር በኅብረተሰቡ ውስጥ እርስ በርስ የተሳሰሩ ዝምድናዎችን፣ ሰላምንና እርስ በርስ የመረዳዳትን መንፈስ ያጎናጽፋል ፡፡

**ተግባራት 2.4**

1.ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ከማነቃቂያ ጥያቄ መልሳችሁ ጋር አመሳክሩ፡፡
2.ሌሎችን ማክበር ለእናንተ ስለለው አስተዋፅኦ ተወያዩ፡፡

**አንድ አንድ የማህበረሰቡ ክፍሎችን የማክበር አስፈላጊነት**

### 2.3.1. ታላላቆችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

*በአከባቢያችሁ የሚገኙ ታላላቅ ሰዎችን ልትጠቅሱ ትችላላችሁ?

ታላቅ ማለት ከእኛ በዕድሜ የሚበልጥ ማንኛውም ሰው ነው ፡፡ ከእነዚህም መካከል ከእናንተ በዕድሜ የሚበልጡ ወንድሞች፣ እህቶች፣ የክፍል ጓደኞችና ጎረቤቶች ይገኙበታል፡፡ በዕድሜ የገፉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ “ታላላቆች” ተብለው ይጠራሉ፡፡ ለምሳሌ እናቶች፣ አባቶች፣ የወንድ አያት፣ የሴት አያት፣ ወዘተ በህብረተሰቡ ውስጥ በእድሜያቸው ብቻ ሳይሆን በአቋማቸው፣ በአደረጉት አስተዋፅኦና በማህበራዊ ተቀባይነታቸውም ጭምር በህብረተሰቡ ውስጥ በታላቅነት እውቅና ያገኙ አንዳንድ ሰዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል የማኅበረሰቡ መሪዎች ፣ የሃይማኖት መሪዎችና የተከበሩ ሰዎች ታላላቆች ናቸው ፡፡

ተግባር 2.5

1. ከላይ ከተዘረዘሩት ታላላቆች ሰዎች ውስጥ ምን ያህሉን መጥቀስ ትችላላችሁ?
2. በክፍል ውስጥ ብታገኟቸው እንዴት ምላሽ እንደምትሰጡ ሃሳባችሁን አካፍሉ፡፡

ታላላቆችን ማክበር በዕድሜ ለገፉ ሰዎች እንዲሁም ለማኅበረሰቡና ለሃይማኖት ተቋማት መሪዎች አክብሮት ማሳየትን ይጨምራል፡፡ ይህም ለታላላቆቻችን ያለንን አክብሮት ያሳያል ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ "ታላላቆችን አድምጡ!" የሚል የጋራ የሞራል መርህ አለው፡፡ ይህም ታላላቆቻችንን ምንጊዜም ማክበርና ማዳመጥ አለብን ማለት ነው ፡፡

ታላላቆችን ማክበር ማለት ፡-

- እነሱን ስታገኟቸው ጨዋ መሆን ፤ሲመክሩን በጥሞና ማዳመጥ፤
- ለእነሱ በጎ ነገር እንድታደርጉላቸው ሲጠይቁ በአክብሮትና በትህትና ምላሽ መስጠት፤
- በሚናገሩበት ጊዜ አለማቋረጥ፤ከእናንተ ድጋፍ ያስፈልጋቸው እንደሆነ መጠየቅ እና
- እነሱን ማድነቅና ማክበር ነው፡፡



ምስል 2.3. ለታላላቆች ቅድሚያ መስጠት

ተግባር 2.6

1. ከላይ ካለው ስዕል ምን ተማራችሁ?
2. ይህን በማድረጋችሁ ደስተኞች ናችሁ?
3. በማህበረሰባችሁ ውስጥ ብዙውን ጊዜ የተለመዱ እንደ ‘ታላላቆችን ማዳመጥ’ ያሉ የሥነ ምግባር መርሆችን አካፍሉ፡፡

## 2.3.2.የሃይማኖት አባቶችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

* የሃይማኖት አባቶቻችሁን ስም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

የሃይማኖት አባቶች በእምነት ውስጥ ያሉ መሪዎች ናቸው ። በተጨማሪም በሃይማኖታዊ ተቋማት ውስጥ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የሀይማኖት አባቶች መጠሪያና ተግባር በየሃይማኖታቸው የተለያየ ነው። የሃይማኖት መሪዎች ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ኢማሞችና ፓስተሮች ይገኙበታል። ብዙውን ጊዜ በማኅበረሰባቸው ውስጥ በጣም የተከበሩ ሰዎች ናቸው ።



ምስል 2.4: የሐይማኖት አባቶችን ማክበር

የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በርካታ ተግባራት አሏቸው እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

- ሃይማኖታዊ ደንቦችን ማስተማርና መስበክ፣
- ለማህበረሰቡ መልካም ባህሪ እንዲኖረው መምከር፣
- በግጭት ውስጥ ያለዉን ህዝብ ማስታረቅ፣ እና
- የግለሰቦችን ምግባር ተቀባይነት ባለው መንገድ መቅረጽ፣ ወዘተ

ስለዚህ የሃይማኖት አባቶችን ማክበር ማለት፡-

- ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ክብር ግምት ውስጥ ማስገባት እና ምክራቸውን በአካልም ሆነ በቡድን መቀበል፣
- የሚያዙትን ለመስማት ፈቃደኛ መሆን፣
- ምክራቸውን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ ወዘተ ማለት ነው።

ተግባር 2.7

1. የሃይማኖት አባቶቻችሁን ታከብራላችሁ?
2. የሃይማኖት አባቶችን የማክበር አስፈላጊነት ላይ ተወያዩ::

### 2.3.3 መምህራንን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

* የሚያስተምሯችሁን መምህራን ስም ጥሩ?



ምስል 2.5. በክፍል ውስጥ መምህራንን ማክበር

ተግባር 2.8

1. ከላይ ካለው ስዕል ምን ትማራላችሁ?
2. በክፍል ውስጥ ካለው ተሞክሮ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት አለው?
3. መምህራንን ስለማክበር ምን እንደሚሰማችሁ ተናገሩ::

መምህራን እናንተን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩ የእውቀት አባቶች ናቸው :: መምህራን የተማሪዎችን ባህሪ እና ተቀባይነት ያላቸውን የማህበረሰብ ደምቦች በመቅረፅ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው:: በተለይ ተማሪዎች እና ወላጆች ለመምህራን አክብሮት መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው :: ይህም ከመምህራን ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ያደርጋል:: ከመምህራን ጋር ያላችሁ መልካም ግንኙነት በባህሪያችሁ እና በትምህርታችሁ ስኬትማ እንድትሆኑ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤቱ ውጪ ለመምህራን ትሁት ልትሆኑ ይገባል:: የሚሰጧችሁን ምክር በማዳመጥና በተግባር ላይ በማዋል ጠባያችሁን ለመለወጥ ልትጠቀሙበት ይገባል:: መምህራንም ተማሪዎቻቸውን መውደድ እና ማክበር ይጠበቅባቸዋል::

## 2.3.4.ቤተሰብን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

*የቤተሰቦቻችሁን ስም ዘርዝሩ?

ቤተሰብ ማለት አብረው በቤት ውስጥ የሚኖሩ የግለሰቦች ስብስብ ነው። በተጨማሪም በዝምድናም ሊገለጽ ይችላል ። በሌላ አነጋገር ቤተሰብ ማለት የጋራ ቅድመ አያቶችን የሚጋሩ ሰዎች ስብስብ ነው ። እንደ ማህበራዊ ክፍል ቤተሰብ ማለት ወላጆችና ልጆችን ያካተተ ነው ። ለምሳሌ እናንተ፣ እናታችሁ፣ አባታችሁ፣ እህቶቻችሁና ወንድሞቻችሁ አንድ ላይ ሆናችሁ ቤተሰብ ተብላችሁ ትጠራላችሁ።



ምስል 2.6. ቤተሰብን በማገዝ ማክበር

የቤተሰብ አባላትን ማክበር ይኖርባችኋል። የቤተሰብ አባልን ማክበር የሚጀምረው ለቤተሰብ አባላት ጥልቅ አድናቆት በማሳየት ነው። ስለዚህ የቤተሰብ አባልን መውደድ በጣም አስፈላጊ ነው። በቤተሰብ አባላት መካከል ፍቅርና ስምምነት ከሌለ በቤት ውስጥ አስደሳች ህይወት አይኖርም ። አክብሮትና ፍቅር በጣም አስፈላጊ የሆኑ የቤተሰብ መሰረቶች ናቸው።

ለቤተሰብ አክብሮት ማሳየት የምንችልባቸው አንዳንድ መንገዶች አሉ። እነሱም ትሕትና ማሳየት፣ ሌሎችን መርዳት ፣ ምክራቸውን ማዳመጥ እና ውሳኔያቸውን መቀበል ናቸው።

**ተግባር 2.9**

1.ቤተሰባችሁን ታከብራላችሁ?

2.ቤተሰብን እንዴት እንደምታከብሩ ተሞክሯችሁን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ።.

3.ቤተሰብን ማክበር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ጥቀሱ።

## 2.3.5. ጎረቤቶችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

*ቢያንስ የአምስት ጎረቤቶቻችሁን ስም ልትጠቅሱ ትችላለችሁ?

ጎረቤቶቻችሁ በቤታችሁ አቅራቢያ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። ጎረቤቶች በአቅራቢያችሁ በሚገኝ ቤት፣ አፓርታማ ወይም የጋራ መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። ጎረቤቶቻችሁ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የቤተሰቦቻችሁን አባላትና እናንተን ሊደግፉ ይችላሉ። ጥሩ ጎረቤቶች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ተባብረው ሊሰሩና ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥማችሁ ሊረዷን ይችላሉ።



ምስል 2.7. ጎረቤትን ማክበር

ጎረቤቶቻችንን ማክበር ሰላማዊ ህይወት ለመኖር ቅድመ ሁኔታ ነው። በተጨማሪም ከጎረቤቶቻችን ጋር ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር ተባብሮ ለመኖር መሠረት ነው ። በእናንተና በጎረቤቶችሁ መካከል ያለው መቀራረብ ማህበራዊ ህይወትን ያበረታታል እናም ጥሩ ግንኙነት ይፈጥራል።

ይህ ደግሞ በበኩሉ በአንድ ሀገር ውስጥ ሰላማዊ የሆነ ማህበረሰብ እንዲኖር ያደርጋል። ለጎረቤቶቻችን አክብሮት የምናሳይባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ለጎረቤቶቻችሁ ሰላምታ መስጠት፣
- ከጎረበቶቻችሁ ጋር መገናኘትና ስማቸውን ማወቅ፣
- ከጎረቤቶቻችሁ ጋር መቀራረብ፣
- የማህበረሰባችሁ ንቁ አባል መሆን፣
- አካባቢያችሁን ንጹሕ ማድረግና
- ጎረቤቶቻችሁን አለመረበሽ ወይም ድምፃችሁን መቀነስ።

**ተግባር 2.10**

1. ለጎረቤቶቻችሁ አክብሮት የምታሳዩባቸውን መንገዶችን ጥቀሱ።
2. በክፍል ውስጥ ጎረቤቶቻችሁን እንዴት እንደምታከብር አሳዩ።
3. ጎረቤቶቻችሁን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## 2.3.6.የክፍል ጓደኞችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

* ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተገቢውን አክብሮት ወይም ክብር ትሰጣላችሁ?

በክፍላችሁ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በሙሉ የክፍል ጓደኞቻችሁ ናቸው:: በሌላ አነጋገር በአንድ ትምህርት ቤት በተመሳሳይ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ከተለያየ የኑሮ ሁኔታ የመጡ ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ የእናንተ ጥሩ ጓደኞቻችሁ ናቸው:: አንዳንዶቹ ከድሃ ቤተሰብ ሌሎቹ ደግሞ ሀብታም ከሆነ ቤተሰብ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ:: ከዚህም በላይ የክፍል ጓደኞቻችሁ የተለያየ የቆዳ ቀለም፣ ሃይማኖታዊ አስተዳደግና ቋንቋ አላቸው:: አንዳንዶቹ የክፍል ጓደኞቻችሁ በትምህርት ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ሲያስገኙ፤ ሌሎቹ ደግሞ ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ ውጤት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ሁሉም በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው:: ጠዋት ላይ የክፍል ጓደኞቻችሁ ስታገኟቸው ምን ታደርጋላችሁ?



ምስል 2.8 የክፍል ጓደኞቻችንን ማክበር

የክፍል ጓደኞቻችሁን ማክበር ቀደም ሲል የተጠቀሱትን በመካከላችሁ ያሉ ልዩነቶችን መቀበል እንዲሁም ከእነሱ ጋር ጥሩ ዝምድና መመሥረትን ይጠይቃል:: ጥሩ ግንኙነት መመሥረት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ጥሩ ወዳጅነት ለመመሥረት ያስችላችኋል:: ጓደኝነት መመስረት አብራችሁ እንድትጫወቱ፣ በአንድ ላይ እንድታጠኑ እንዲሁም አብራችሁ እንድትበሉና እንድትጠጡ ያስችላችኋል:: ይህ ደግሞ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ብልህና ንቁ ተማሪ እንድትሆኑ ይረዳችኋል :: ስለዚህ በክፍል ውስጥ እርስ በርስ መከባበር ከሁሉ የተሻለና ፍሬያማ ወዳጅነት ለመመሥረትና በትምህርታችሁ ስኬታማ ለመሆን የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ ነው:: የክፍል ጓደኞቻችሁን ማክበር የምትችሉባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፦

- ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትገናኙ ሞቅ ያለ ሰላምታ መለዋወጥ፣
- ከጓደኞቻችሁጋር በምትነጋገሩበት ጊዜ በጥሞና ማዳመጥ፣
- ከሌሎች ጋር በምትጨዋወቱበት ጊዜ ትኩረት መስጠት እና አለማዋረድ፣
- በጥሩ ሁኔታ ማስተናገድና አድናቆትህን መቸር እንዲሁም
- ለስሜታቸውና ለደህንነታቸው ጥንቃቄ ማድረግ ናቸው።

ተግባር 2.11

1. ጓደኞቻችሁን ምን ያህል እንደምታከብሯቸው ንገሯቸው።.
2. በክፍል ውስጥ እርስ በርሳችሁ የምትከባበሩበትን መንገድ አሳዩ።.
3. አንዳችሁ ለሌላችሁ ያላችሁን አክብሮት ግለጹ።

## 2.4. የተከበሩ ሰዎች ባህርያት



የማነቃቂያ ጥያቄ

*የተከበሩ ሰዎችን ባህሪያት ዘርዝሩ።

ባሕርይ የአንድ ሰው ልዩ መገለጫ ነው። ቀደም ባሉት ትምህርቶች ላይ ሰዎችን የምታከብሩበት የተለያዩ መንገዶችን ተምራችኋል። እንዲህ ዓይነት መንገዶችን መከተል የተከበራችሁ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል።



ምስል 2.9. የተከበሩ ሰዎች ባህርያት

የተከበሩ ሰዎች እንደ ጨዋነት፣ ትሕትና፣ ክብር የመስጠት፣ ተንከባካቢነት፣ሐቀኝነት፣ኃላፊነት ፣እንደ ሁኔታው የመለዋወጥ፣ ትዕግሥት ወይም መቻቻል ፣ እንዲሁም ጥሩ አድማጭና አፍቃሪ የመሆን ባሕሪያት አሏቸው።

ተግባር.1.2

1. የተከበሩ ሰዎች ባህርያትን ጥቀሱ?
2. ለሌሎች አክብሮት በማሳየት ረገድ ያላችሁን ባሕርያት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።.

## 2.5. ለሌሎች ክብር መንፈግ የሚያመጣው ተጽዕኖ

የማነቃቂያ ጥያቄ

* ሌሎችን የማክበር ተቃራኒ ምንድን ነው?

የማክበር ተቃራኒው አለማክበር ወይም ክብርን መንፈግ ነው፡፡ክብር መንፈግ ማለት በአጠቃላይ ክብር አለመስጠት ነው፡፡ ክብር መንፈግ ማለት ለአንድ ሰው ያለንን አድናቆት እና ትህትና መንፈግ ነው፡፡ እንዲሁም ለሌሎች ሰዎች ስሜት፣ ፍላጎት፣ ነፃነት፣ ክብር፣ ሰብዓዊነት ወይም ማህበራዊ ጉዳይ ግድየለሽ መሆን ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ሌሎችን መሳደብን፣ባለጌነትን ፣ ትህትና የጎደለው ድርጊትን ፣ መጥፎ ድርጊትን ወይም ጠባይን ያካትታል፡፡



ምስል 2.10. ሌሎችን አለማክበር

እንደዚህ ዓይነት ባህርያት እና ተግባራት በርካታ ተፅዕኖዎች ያመጣሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- በሰዎች መካከል ትህትና እና መከባበር እንዳይኖር ያደርጋሉ፣
- በሰዎች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ይሸረሽራሉ፣
- ተባብሮ የመስራት ባህልን ያጠፋሉ፣
- ለግለሰቦች የምንሰጠውን እንክብካቤ ይቀንሳሉ፣
- ጓደኝነት ላይ ተፅዕኖ ያመጣሉ፣
- ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት እና ጥላቻ እንዲኖር ያደርጋሉ፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ በሰላም የመኖር ባህልን ያጠፋሉ ፡፡

**ተግባር 2.13**

1. እራስን እና ማህበረሰብን አለማክበር የሚያስከትለውን ተፅእኖ ዘርዝሩ፡፡
2. ሌሎችን የማክበር እና ያለማክበር ፅንስ ሀሳብቦችን አወዳድሩ እና ሰዎችን አለማክበር ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ተናገሩ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ ሌሎችን ስለማክበር ነው፡፡ የሰውን ክብር ዋጋ በመስጠት ይጀምራል፡፡ ሰላምታ፣ትህትና፣ ጥሩ አድማጭ መሆን እና የመሳሰሉት ባህርያት ሌሎችን እንዴት ማክበር እንዳለብን የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ታላላቆች፤ አባቶች፣ እናቶች፣ አያቶችን፣ ወዘተ ጨምሮ ክብር ያስፈልጋቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖታዊ አገልግሎት የሚሰጡ የሃይማኖት አባቶችንም ማክበር አለብን፡፡ መምህራን እናንተን እና ህብረተሰቡን የሚያስተምሩ ምሁራን ስለሆኑ በወላጆች እና በተማሪዎች መከበር አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የቤተሰብ አባላትን፣ ጎረቤቶችን፣የክፍል ጓደኞቻችሁን፣ በትህትናና በታማኝነት ክብር ማሳየት ወሳኝ ነገር ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

**ክብር:** ስለ አንድ ሰው አስፈላጊነት ያለን መረዳት እና ስሜት ነው፡፡
**ጎረቤት:** ከእናንተ ቤት ወይም ከሌላ ሰው ቤት አጠገብ የሚኖር ሰው ማለት ነው፡፡
**ዝምድና:** ማለት በቤተሰባችሁ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር በደም ወይም በቃል ኪዳን የመተሳሰር ሁኔታ ነው፡፡
**የተከበረ:** ክብር የሚገባው ማለት ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች

**ክፍል አንድ: ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. ሌሎችን ማክበር ለራስ ብቻ ክብር የሚሰጥበት መንገድ ነው።
2. ከእናንተ በዕድሜ የሚበልጡ ሰዎች ከእናንተ አክብሮትን ይሻሉ።
3. የሃይማኖት መሪዎች በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው።
4. ጎረቤትን ማክበር ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።
5. ሌሎችን አለማክበር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የግጭት ምንጭ ሊሆን አይችልም።

**ክፍል ሁለት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ሌሎችን በማክበር ረገድ ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. ለሰው ክብር መስጠት
   - ለ. አመስጋኝ መሆን
   - ሐ. የሌሎችን ሀሳብ መናቅ
   - መ. ትሁት መሆን
2. ታላላቆችን በማክበር ረገድ ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ከሰዎች ጋር ስንገናኝ ትሁት መሆን
   - ለ. ሰዎች ሲያወሩ ጣልቃ መግባት
   - ሐ. ለሰዎች በአክብሮት ምላሽ መስጠት
   - መ. የታላላቆችን ምክር መቀበል
3. ከሚከተሉት ውስጥ ሌሎችን የማክበር ባህሪ የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ብልግና
   - ለ. ሌሎችን ችላ ማለት
   - ሐ. ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት
   - መ. ሌሎችን ማዳመጥ
4. ከሚከተሉት ውስጥ ክብር የመንፈግ ባህሪ ተፅዕኖ የትኛው ሊሆን ይችላል?
   - ሀ. የመተባበር ባህልን መጉዳት
   - ለ. ጥላቻን ማበረታታት
   - ሐ. ሰላማዊ አብሮነትን ችላ ማለት
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው

**ክፍል ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ጻፉ።**

1. ታላላቆችን ከማክበርያ መንገዶች መካከል ቢያንስ ሶስቱን ጥቀሱ።
2. ሌሎችን ከማክበር ጥቅሞች መካከል ቢያንስ ሶስቱን ጻፉ።
3. ሌሎችን አለማክበር የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ዘርዝሩ።

# ምዕራፍ ሦስት

# እኩልነት

ምዕራፍ ሦስት: እኩልነት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች: ተማሪዎች ከምዕራፉ መጠናቀቅ በኃላ:

- እኩልነትን ታብራራላችሁ፣
- በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ በእኩል የማየትን ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ፣
- ፍትሀዊነትን ከትምህርት ቤትና ከማህበረሰቡ አንጻር ታብራራላችሁ፣
- የግለሰቦች ወይም የቡደኖች በእኩል አለመታየት የሚያመጣውን ተፅእኖ ታብራራላችሁ።.

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የእኩልነትን ትርጉም ያስተዋውቃችኋል። እንዲሁም በትምህርት ቤት እና በማህበረስብ ውስጥ የእኩልነትን ጠቀሜታ በተመለከተ ግንዛቤ ይፈጥራል። እንደ የፆታ እኩልነት፣የቋንቋ እኩልነት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የባህል እኩልነት ያሉ የእኩልነት መሰረታዊ ነጥቦች በሰፊው የሚቀርብበት ነው። በመጨረሻም ይህ ምዕራፍ በእኩል ዓይን የማየትን ጥቅም እና በእኩል አለማየት የሚያሰከትለውን ተፅዕኖ ይዳስሳል።

## 3.1. እኩልነት ምንድነው?

**የማነቃቂያ ጥያቄ**



- *እኩልነት የሚለውን ቃል ለመጀመርያ ጊዜ ስትሰሙ ቶሎ ወደ አዕምሯችሁ የሚመጡት ሀሳቦች ምንድን ናቸው?
- *እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

**እኩልነት፡-** ማለት ተመሳሳይ ደረጃ ላላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እኩል መብት እና ጥቅሞችን መስጠትን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም እኩልነት ሰዎች ሃላፊነታቸውን በእኩል መወጣት እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ ለምሳሌ አንድ "ሰው" ሰው በመሆኑ ብቻ የተወሰኑ መብቶች አሉት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፤ እኩል ሙያና ደረጃ ያላቸው ግለሰቦች እኩል ጥቅሞችን የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

**እኩልነት፡-** ማለት ሌሎች ሰዎች ሊኖራቸው በሚችለው ልክ አንድ ዓይነት መብት፣ ክብር እና ነፃነት ለሌሎች ሰዎችም መስጠት ማለት ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል በሌሎች ዘንድ የመከበር መብት፣ ሀብት እና ትምህርት የማግኘት መብት እንዲሁም ከሌሎች እኩል የወደፊት ህይወታችሁን የመምረጥ ነፃነት ይገኙበታል፡፡

**እኩልነት፡-** እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቡድን ለዜጎች የእኩልነት መብቶች እና እድል ማመቻቸትን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በማህበራዊ አቋም ወዘተ የእኩልነት መብት ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

### ስለ ህፃናት እኩልነት የሚገልፅ ትረካ
### ሰዎችን በማንነታቸው መቀበል

**ቡቤ** በትምህርት ቤት ውስጥ በጣም ታዋቂ ልጅ ነበር ፡፡ በጣም ውድ በሆነ ጫማው፣ ሱሪው እና በሀብታም ልጅነቱ ይታወቅ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በሁሉም ሰው ዘንድ በጣም የተከበረና የተደነቀ፤ ውድ በሆኑት አሻንጉሊቶቹ እና ልብሶቹ በትምህርት ቤት ያሉትን ልጆች ለማስደመም በቂ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ ጓደኞችን በሚመርጥበት ጊዜ አንዳንድ መሥፈርቶችን ይከተል ነበር፤ በመሆኑም ወደ ቡድኑ መግባት የቻሉት ሰዎች በጣም የተከበሩ እንደሆኑ ይሰማቸው ነበር ፡፡

**ቡቤ-** “ወዳጄ ለመሆን የተወሰነ ደረጃ ሊኖርህ ይገባል፡፡ አስቀያሚ፣ አሳዛኝ ወይም ድሃ ከሆንክ እባክህ ጊዜዬን አታባክን፡፡” ይል ነበር፡፡

አንድ ቀን ዱዱ የተባለ አዲስ ልጅ ወደ ትምህርት ቤቱ ሲገባ ሁኔታዎች

መለወጥ ጀመሩ:: የማሰብ ችሎታውና ሁለገብ ባሕርይውም ሁሉንም ሰው መሳብ ጀመረ:: ከመጀመሪያው ፈተና በኋላ በትምህርቱ እና በትምህርት ቤት ውስጥ በሚከናወኑ የክበባት እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፉ ታዋቂ ሆነ:: አሁን ሁሉም ሰው የዱዱ ጓደኛ መሆን ፈለገ:: ከቡቤ በተለየ መልኩ ዱዱ ለጓደኞቹ ያን ያህል መሰፈርት አልነበረውም:: ቡቤ ልደቱ ከመከበሩ ከሁለት ቀን በፊት የቅርብ ጓደኛው ማና መጣች እና “ዱዱንም መጋበዝ አለብህ:: አዝናኝ እኮ ነው::” ስትል ጠየቀችው::

ቡቤም: “አይሆንም! የሚለብሰውን አለባበስ ተመልከች:: ቆሻሻ የሚያነሳ ይመስላል:: ይህን ርካሽ የምሳ እቃ እና ምንም የማይጣፍጥ ምግብ ወደ ትምህርት ቤት ይዞ ይመጣል:: ከእኛ ጋር ሊወዳደርም፣ ሊመጥነንም አይችልም::” ሲል መለሰላት::

ማና: “ኦ! አይደለም፣ በጣም ጥሩ ልጅ ነው:: ዕድል ስጠው:: እናንተ እንደ ጓደኛ ልታቀርቡት ትችላላችሁ” በማለት ልታግባባው ሞከረች::

ቡቤም: ያን ያህል በሃሳቧ ባያምንበትም የቅርብ ጓደኛው አጥብቃ ስለጠየቀችው ብቻ “እሺ! ነገር ግን ግብዣውን እንዳያበላሸው እርግጠኛ ከሆንሽ ብቻ ነው::” በማለት ዱዱን ወደ ግብዣው ጋበዘው:: ዱዱ ሲመጣ ግን ግብዣው ያማረ ሆነ:: ማናም “አየህ! ሁሉም ሰው ዱዱን ይወዳዋል::” ስትል ለቡቤ ነገረችው::

ቡቤም “ይህ የሆነው ስለሚያዝናኑለት ብቻ ነው::” ብሎ ከመለሰላት በኋላ ማንም ሰው ባለው ደረጃ ሊመረጥ እንደማይችል ተምሮ ሰዎችን በማንነታቸው መቀበል እንዳለበት ተገነዘበ:: በዚህም ምክንያት ቡቤ ዱዱን ይቅርታ ጠየቀው እና አንድን ሰው በሚለብሰው ወይም በሚበላው ነገር ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ መመልከቱ ፈጽሞ ስህተት እንደሆነ እና የሰው ልጅ በሰበአዊነቱ ብቻ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ተረዳ::

ማናም “ጓደኞቼ አብሮ መሆን አስደሳች ነው! እያንዳንዱን ሰው በማንነቱ መቀበል ወዳጅነትን ያጠነክራል:: ይህ በጣም የሚደንቅ ቡድን ነው ምክንያቱም አብረን በማጥናት ወዳጅነታችንን አጠናክረንበታል::” በማለት ደስታዋን ገለጸች::

ተግባር 3.1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1.ከላይ ከተጠቀሰው አጭር ትረካ ምን ተማራችሁ?

2.አንድን ሰው በማንነቱ መቀበልና ማክበር ጥሩ የግብረ ገብ መስፈርት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 3.2 እኩልነት በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ

የማነቃቂያ ጥያቄ

- እናንተ በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያላችሁን የእኩልነት መብት ጥቀሱ፡፡
- እናንተ በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ያላችሁን የእኩልነት መብት ጥቀሱ፡፡

የሚከተሉት የተማሪ መብቶች በክፍልም ሆነ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መከበር አለባቸው፤ እነዚህም፡- ጥያቄ የመጠየቅ መብት፣ ለጥያቄዎቻቸው መልስ የማግኘት መብት፣ ከትምህርት ሰዓት ውጭ በሚከናወኑ ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ መብት፣ በሚመለከቷቸው ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት እና የትምህርት ቤት ንብረትን የመጠቀም መብት ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ተማሪ ኃላፊነቱን በተገቢው መንገድ መወጣት አለበት ፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ የትምህርት ቤት ህግና ደንቦችንና ማክበር፤ ለሌሎች አርዓያ መሆን፤ የቤት ሥራዎችን እና የክፍል ሥራዎችን በሰዓቱ መስራት አስፈላጊ ከሆኑት ኃላፊነቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ተግባር 3.2.

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ መከበር ያለባቸው የተወሰኑ መብቶችን ጥቀሱ፡፡

2. በትምህርት ቤት ውስጥ ልትወጡት የሚገባችሁ ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

### 3.2.1. የፆታ እኩልነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

* የወንዶችና የሴት ልጆች እኩልነት ስንል ምን ማለታችን ነው?



ምስል 3.1 የወንድ እና ሴት እኩልነት

የፆታ እኩልነት የሚያመለክተው ወንዶች እና ሴቶች ከመብታቸው አኳያ እኩል እድል ካላቸው ነው። ይህም ልጃገረዶች እና ወንዶች ልጆች እኩል መሰረታዊ መብቶች እና እኩል እድል ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው። ለምሳሌ ትምህርት የማግኘት፣ የመጫወት፣ የስራ ዕድል የማግኘት፣ የመምረጥ፣ የመመረጥ እና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ የመስራት መብት አላቸው። ስለዚህ ሴቶች በአካልም በአዕምሮም ከወንዶች ጋር እኩል ናቸው። ሴቶች የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ስለሆኑ የፆታ እኩልነትን መቀበልና ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ ከፆታ እኩልነት የተዛባ አመለካከት ጋር መታገል አለበት፤ እንዲሁም የሴቶችን የእኩልነት መብት መቀበልና መደገፍ ይኖርበታል።

ልጃገረዶች ሕይወታቸውን እንዲመሩ፣ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ፣ የወደፊት ዕጣቸውን ፈንታቸውን እንዲወስኑ፣ በአጠቃላይ አቅማቸውን እነዲያጎለብቱ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም ሁሉም ሰው ይጠቀማል። የፆታ ጭቆናን የታገሉ ኅብረተሰቦች ይበልጥ የተረጋጉ፣ አስተማማኝ እና የበለፀጉ፣ ደስተኛ እና የተሻለ ትምህርት ያላቸው ዜጎች እንደሆኑ ታሪክ ይጠቁማል።

ስለ ፆታ እኩልነት ስናነሳ የምናወራው፦

- በወንዶች እና በሴት ልጆች መካከል ያለውን የትምህርት ዕድል ልዩነት ስለመቀነስ፣
- በወንዶች እና በሴቶች መካከል በፖለቲካ ተሳትፎ እና በስራ እድል ያለውን ልዩነት ስለመቀስ፣
- ሴቶች እና ልጃገረዶች መብታቸውን እንዲጠቀሙበት ስለ መደገፍ ነው።

ጾታ በወንዶች እና በሴቶች መካከል በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያለውን ልዩነት የሚያወሳ ነው። ቀደም ሲል ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሀብትን የመጠቀም እኩል መብት አልነበራቸውም። እንዲሁም እኩል የሆነ ትምህርት የማግኘት እና በፖለቲካ የመሳተፍ መብት አልነበራቸውም።

### ተግባር 3.3

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ:**

1. በተለምዶ የሴቶች እና የወንዶች ተብለው የተመደቡትን ስራዎች ጥቀሱ።
2. ወንዶች ሴቶች የሚሰሩትን ስራ ማከናወን ይችላሉ?
3. ሴቶች በተለምዶ የወንዶች ስራ ተብለው የሚታሰቡትን ስራዎች መስራት ይችላሉ?

## 3.2.2. የቋንቋ እኩልነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* የቋንቋ እኩልነት ስንል ምን ማለታችን ነው?

ቋንቋ ለባሕል ዋና መለያ ነው። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ቋንቋዎችን እንደ መግባቢያ ይጠቀሙበታል። የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችንን እና ውስጣዊ ስሜታችንን ለመግለጽ ቋንቋን እንጠቀማለን። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በሙሉ እኩል ናቸው። ስለሆነም ቋንቋቸው በሌሎች ዘንድ እንዲከበርላቸው ይፈልጋሉ። ይህም ማለት የራሳቸውን ቋንቋ ለመማርያነት፣ ለፈጠራ ጽሑፍ እንዲሁም ለሥነ ጽሑፍ መሣሪያነት አድርገው የመጠቀም መብት አላቸው ማለት ነው።

በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሐሳባቸውን የመግለጽና በቋንቋቸው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው ። ከዚህም በላይ ሰዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎችን የመማር መብት አላቸው።

በኢትዮጵያ የራሳቸው የሆነ ልዩ ባህል ያላቸው ብዙ ብሔረሰቦች አሉ። ለምሳሌ ያህል ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ በቤተሰብ እና በአካባቢ ከሚኖሩ ሌሎች ሰዎች የሚነገረውን ቋንቋ ተምረናል። በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስንናገር ምቾት ይሰማናል። ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ሌሎች ሰዎችም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲናገሩ የሚሰማቸው ስሜት ተመሳሳይ ነው።

ሁሉም ቋንቋዎች እኩል እና አስፈላጊ ናቸው። ስለዚህ ሌሎች ሰዎች የሚናገሯቸዉን ቋንቋዎች ማክበር አስፈላጊ ነዉ። ይህም የተለያየ ባሕል ያላቸውን ሰዎች እኩል እና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለማስተናገድ ይረዳል ።

**ተግባር 3.4**

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ:**

1. ሁሉም ቋንቋ እኩል ይመስላችኋል? ለምን? በዚህ ጉዳይ ላይ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት ።
2. በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሰዎች የሚናገሯቸዉን ቋንቋዎች ዘርዝሩ።

## 3.2.3. የሃይማኖት እኩልነት



ምስል 3.2. የተላያዩ የሃይማኖት ተቋማት

የማነቃቂያ ጥያቄ

* የሃይማኖት እኩልነት ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሃይማኖት የተለየ የእምነትና የአምልኮ ሥርዓት ያለው ተቋም ነው። ሃይማኖት ለአንድ ማኅበረሰብ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የማኅብረሰቡ አባላት እርስ በርሳቸው እና ከውጭ ሰዎች ጋር በሚገናኙበት መንገድ ላይ አወንታዊ ተፅእኖ ያደርጋል። የሃይማኖት እኩልነት እያንዳንዱ ዜጋ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል እንዲሁም የእምነቱን ህግ የማስተማርና የመስበክ መብት እንዳለው ያሳያል።

ይህንንም በማድረግ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሃይማኖት መናቅ አይፈቀድለትም። ከዚህ ይልቅ ሁሉም ሰው በመተባበር እና በሰላም መኖር ይጠበቅበታል። ሀገራችን በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ተከባብሮ በሰላም አብሮ የመኖር ረጅም ታሪክ አላት። እያንዳንዱ ዜጋ የሃይማኖት ነፃነት ከሌለው ሰላማዊ አብሮነት አለ ለማለት ያስቸግራል።

ማንኛውንም ሃይማኖት የመከተል መብትን ማክበር፡- ለመረጋጋት፣ ለደህንነት፣ ለሰላም እና ለእድገት ዋስትና ነው። ኢትዮጵያውያን የተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ በመካከላቸውም እርስ በርስ የመከባበር ባህል አላቸው። ክርስትና፣ እስልምና እና ሀገር በቀል የሆኑ (እንደ ዋቄፈና) ወዘተ ያሉ ሀይማኖቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ስለዚህ ሁሉም ሰው እነዚህ ሃይማኖቶች አንዳቸውም ቢሆኑ ከሌላው እንደማያንሱ እና እንደማይበልጡ መረዳት አለባቸው። በመሆኑም ሁሉም ሃይማኖቶች ለምእመናኑ እኩል ጠቀሜታ አላቸው።

ስለዚህ ማንኛውም ሰው የሌሎችን መብት ሳይነካ ሃይማኖቱን የመከተል መብት አለው።

የጋራ መግባባትን ለማሻሻል የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ጠቃሚ ነው፦

- የሌሎች ሰዎችን ሃይማኖት ማክበር እና ልዩነቶችን በውይይት መፍታት።
- ልዩነቶችን በውይይት መፍታት አስቸጋሪ ከሆነ ቀጣዩ አማራጭ በህግ መሰረት መሄድ እነዲሁም
- ሃይማኖት አብሮ ለመኖር እንቅፋት እንዳይሆን የመቻቻልን ባህል ማዳበር ናቸው።

ተግባር 3.5

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ:**

1. የሁሉንም ሃይማኖት በእኩልነት ማክበር ምን ጥቅም አለው?
2. የሃይማኖት እኩልነትን በተመለከተ የዜጎች ኃላፊነት ምንድን ናቸው?
3. የሃይማኖት አለመቻቻል ለጋራ ጥቅም ጎጂ ነው ብላቹህ ታስባላችሁ?
4. በሃይማኖታዊ አስተምሮ አለመግባባት ምክንያት ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችን እንዴት ማስወገድ ወይም መቀነስ እንችላለን?

## 3.2.4. የባህል እኩልነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* የባህል እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

ተማሪዎች! ከሚከተለው ሥዕል ምን ተረዳችሁ?



ምስል 3.3: የተለያዩ ባሕሎችን የሚያሳይ ሥዕል

ባህል የአንድ ማህበረሰብ የአኗኗር ዜይቤ ነው። ቋንቋ እና ሃይማኖት የባህል መገለጫዎች ናቸው። በተጨማሪም የሐዘን እና የደስታ አገላለጽ፣ በንግግር፣ በአለባበስ እንዲሁም በአመጋገብ ይገለጻል ።

ባህል እኩል አያያዝን የሚጠይቅ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። የኢትዮጵያ የባህል ልዩነት ከአካባቢ አካባቢ ይለያያል። የትኛውም ባህል ከየትኛውም ባህል የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም። ባህል ቋሚ አይደለም፤ በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ በሚያጋጥሙ ለውጦች እና በተፈጥሮ ሁኔታዎች ሊለወጥ ይችላል።

በኢትዮጵያ እንደ ቋንቋ እና ሀይማኖት የራሳቸው ባህል ያላቸው ብዙ ቡድኖች አሉ። እንዲሁም ብዙ ዓይነት የባህል አልባሳት፣ ቋንቋዎች፣ ባህላዊ ቤቶች፣ የባህል ምግቦች እና የባህል ጭፈራዎች አሉ። እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም ግን ሁሉንም ባሕሎች እኩል ማየት አስፈላጊ ነው። የተለያዩ ቋንቋዎች፣ አልባሳት እና ጭፈራ ያላቸው ከ80 በላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረ-ሰቦች አሉ። እነዚህ ሁሉ መልካም ባህላዊ ልማዶች በተለይ አብረው ሲታዩ በጣም ውብ እና ማራኪ ናቸው።

ተግባር 3.6.

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ:**

1. ባህል ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ማህበረሰቦች የሚተገብሯቸውን ባህላዊ ልማዶችን ዘርዝሩ::
3. የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጡ፦ ከዚያም በባህሎቻችሁ ውስጥ የተካተቱ ልማዶችን በተመለከተ መረጃዎችን በመጠቀም የተሰጡትን ባዶ ቦታዎችን ሙሉ::

| ተ.ቁ | ጠቃሚ የሆኑ ልማዶች | ጎጂ ልምዳዊ ድርጊቶች |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |

በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚከናወኑ ባህላዊ ልማዶች መካከል ጥሩም ሆነ መጥፎ ባህላዊ ልማዶች ይገኙበታል::

ሀ. ለዕድገትና ለለውጥ የሚጠቅሙ መልካም ባህላዊ ልማዶች:-

- ታላላቆችን ማክበር፤
- “እድር” እና “እቁብ”፣
- የተቸገሩትን መርዳት፤
- በቡድን መስራት፤
- እንግዳ ተቀባይ መሆን፤ ወዘተ ናቸው::

ለ. ጎጂ ባህላዊ ልማዶች የሚከተሉት ናቸው

- ያለ እድሜ ጋብቻ፣
- ለሐዘን ሲባል ፊትን መንጨት፣
- በስለት ነገር ሰውነትን መቁረጥ፣
- አባካኝነት፣
- ጠለፋ፣ ወዘተ

## 3.3. በእኩል የመስተናገድ ጠቀሜታ



**የማነቃቂያ ጥያቄ**

በእኩል የመስተናገድን ጽንሰ-ሀሳብ አብራሩ?

እኩልነት ማለት:- በማንኛውም ኅብረተሰብ ወይም በአጠቃላይ በዓለም ውስጥ በጣም ወሳኝ ነው:: እኩልነት እኩል መስተናገድ እና እድል ማግኘት ሲሆን፤ ምንም ዓይነት መድልዎ አለመኖሩን ያሳያል::

እኩል መስተናገድ፡- በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔርም ሆነ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በገንዘብ ደረጃ ወይም በትምህርት ደረጃ ላይ ያለ ምንም አድልዎ እኩል ጥቅም፣ እንክብካቤ፣ ፍቅር፣ የትምህርት እድል እና ተሳትፎ ከማግኘት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አድሎአዊነት ለግለሰቦችም ሆነ ለአገር እድገት ወይም ለውጥ ማሳየት አስቸጋሪ ነው፡፡ ሁሉም ሰው እኩል ነው ተብሎ ስለሚታሰብ በተመሳሳይ መንገድ ይሰተናገዳል፡፡ ለምሳሌ ያህል በትምህርት ቤት ውስጥ ማንኛውም ተማሪ በተመሳሳይ መንገድ መስተናገድ አለበት ፡፡ በፍትሃዊ መንገድ የሚሰተናገዱ እና እኩል እድል ያላቸው ሰዎች በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ለማህበረሰቡ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የመቀራረብ ስሜት ሊያዳብሩ፣ የነጻነት ስሜት ሊያድርባቸው እንዲሁም እድገትን እና ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡

ተግባር 3.7.

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ:**

1. በእኩልነት የመስተናገድ ዋና አስፈላጊነትን ዘርዝሩ፡፡.
2. እኩልነት መተግበር ያለበትን ሁኔታ ግለፁ፡፡

## 3.4 አድሎአዊነት የሚያስከትለው ተፅዕኖ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**



- በእኩል አለመኖር አሉታዊ ተጽእኖ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?
- አድሎአዊነት የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተፅእኖዎች ምንድን ናቸው?

አድሎአዊነት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መሰረታዊ መብቶቻቸውን እና እድሎቻቸውን ሲነፈጉ መድልዎ መኖሩን የሚያሳይ ሁኔታ ነው፡፡ አድሎአዊነት ሲኖር ለግለሰቦች እና ለቡድኖች በአንድነት የመኖር እና የሀገራቸውን እድገት ለማፋጠን ሰላም እና መረጋጋት የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና ለማስጠበቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

አድሎአዊነት አንድ ሰው ለራሱም ሆነ ለሌሎች መልካም ነገሮችን የማበርከት ችሎታው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ እኩልነት ሲኖር፣ አድልዊ አሰራር የሚፈፀምባቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች ተረጋግተው ሊቀመጡ አይችሉም፤ ከዚህ ይልቅ መብታቸውን መጠየቅ ይጀምራሉ፤ ይህም ወደ ግጭትና ጦርነት ሊያመራ ይችላል፡፡ አድሎአዊነት በግለሰቦች እና በቡድኖች መካከል ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት እንዲኖር እና የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ግጭት፣ ኢፍትሃዊነት፣ አለመረጋጋት፣ አመፅ እና የመሳሰሉትን አሉታዊ ተፅእኖዎች ሊያስከትል ይችላል፡፡

ተግባር 3.8

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. በሌሎች መገለልን መቀነስ የምንችለው እንዴት ነው?
2. መገለል በስፋት የሚታይባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝሩ።.

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ "እኩልነት" ምን እንደሆነ እና ዓይነቶቹንም ተምራችኋል ። እኩልነት ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነትን አያሳይም። እኩልነት ማለት ተመሳሳይ መብት፣ ጥቅምና እድል ማግኘት ማለት ነው። የእኩልነት መብት መሠረታዊ የሆነ የሰብዓዊ መብት ነው ። መገለል በሌለበት ሁኔታ እኩልነትን ማጣጣም ይቻላል። የኢትዮጵያ ዜጎች እኩል የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ እድል አላቸው። የኢኮኖሚ እኩልነት ማለት፡- እኩል እድል ማግኘት ማለት ነው። ለምሳሌ የሥራ ዕድል።

የፖለቲካ እኩልነት ማለት፡- ሁሉም ዜጋ ለፖለቲካ ተሳትፎ እኩል መብትና እድል ማግኘት ማለት ነው።

ስርዓተ ጾታ፡- በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በወንዶች እና በሴቶች መካከል የሚፈጠር ልዩነት ማለት ነው። የፆታ እኩልነት ወንዶች እና ሴቶች ከመብታቸው አንጻር እኩል እድል እንደሚያገኙ የሚያመለክት ነው ።

ብዝሃ ባህል፡- ብዙ ጥቅሞች አሉት። ምክንያቱም እያንዳንዱ ባህል ለሀገራችን ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። የባሕል ብዘሃነትን ስናከብር ከባሕላችን ጥቅም ማግኘት እንችላለን። የሌሎችን ባሕል አሳንሶ ማየት ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል። ብዝሃነትን ማክበር እና ባህሎችን በእኩል ማየት ያስፈልጋል። ምክንያቱም በአንድነት በመስራት የጋራ ጠላታችን ድህነትን በጋራ እንድንዋጋ ያስችለናል።

**ቁልፍ ቃላት**

- **ባህል፡-** የተወሰኑ ሰዎች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች እምነቶችን ፤የኗኗር ዘይቤን፣ ቋንቋን፣ ሃይማኖትን፣ እና ባህላዊ ልማዶችን ይጨምራል።
- **"ደቦ" ወይም "ወንፈል"፡-** ማለት የገጠር ሰዎች እርስ በእርሳቸው ድጋፍ ለማግኘት በቡድን የሚሰሩበት ልማድ ነው።
- **መገለል-** በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በዘር፣ በእድሜ፣ በቀለም እና በአካል ጉዳተኞች ላይ ሆን ተብሎ እና ያለ አግባብ የሚፈፀም በደል ነው።
- **ብዝሃነት-** ማለት በሃይማኖት፣ በቋንቋ ወዘተ በሰዎች መካከል ያለ ልዩነት ነው።
- **እኩልነት-**ያለ አድልዎ ጥቅማ ጥቅምን የማግኘት እኩል መብትና ግዴታዎችን መወጣት ነው።
- **ስርዓተ ፆታ፡-** በወንዶች እና በሴቶች መካከል ከተፈጥሮ ይልቅ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ መካከል ያለ ልዩነት ነው።
- **ሃይማኖት፡-** ማለት አብዛኛውን ጊዜ ሰውን የሚገዛ ኃይል ከማመን እና ከአምልኮ ጋር የሚያያዝ የተደራጀ እምነት ተቋም ነው።
- **መብት ፡-** ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባ ጥቅም።
- **መረጋጋት፡-** ማህበራዊ ስርዓት እና የሰላም ሁኔታ ነው።

**የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች**

**ክፍል አንድ: ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ “እውነት” ስህተት ከሆነ ደግሞ“ሀሰት” በማለት መልሱ።**

1. እኩልነት በግለሰቦች እና በቡድን መካከል ያለ ተመሳሳይነትን ያመለክታል።
2. ልጆች በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ እኩል መብት አላቸው።
3. የፆታ እኩልነት ከመብት፣ አገልግሎቶችን ከማግኘት እና ከስራ እድል አንፃር የወንዶችን እና የሴቶችን እኩልነት ያመለክታል።
4. ከዴሞክራሲ ባህሪያት አንዱ የቋንቋ እኩልነት ነው።

**ክፍል ሁለት፡ በአምድ ‘ሀ ’ ስር ያሉትን ቃላት ወይም ሐረጎች በአምድ ‘ለ ’ውስጥ ካሉት ትክክለኛ አማራጮች ጋር አዛምዱ፡፡**

| አምድ ‘ሀ | አምድ ‘ለ’ |
|---|---|
| 1.ጤናማ ልምምድ/ስነ-ምግባር | ሀ. የፆታ እኩልነት |
| 2.የወንዶች እና የሴቶች እኩልነት | ለ. ታላላቆችን ማክበር |
| 3.ማንኛውም ሰው የራሱን እምነት የመከተል መብት አለው፡፡ | ሐ. የሃይማኖት እኩልነት |
| 4.የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የማንነት መግለጫ | መ. ቋንቋ |

**ክፍል ሦስት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎችን እኩልነት የማያሳየው የቱ ነው?

    ሀ. ጥያቄ መጠየቅ

    ለ. ግላዊ ሀሳብን በሌሎች ላይ መጫን

    ሐ. ተጨማሪ ተጓዳኝ ተግባራት ላይ መሳተፍ

    መ. በተማሪዎች ጉዳዮች ላይ መሳተፍ

2. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ቋንቋ እውነት የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ሌሎች ቋንቋዎችን መማር ምንም ጥቅም የለውም

    ለ. አንዳንድ ቋንቋዎች ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጣሉ፡፡

    ሐ. ሁሉም ቋንቋዎች ከመግባቢያነት ተግባራቸው አንፃር እኩል ናቸው፡፡

    መ. የቋንቋ እኩልነት ካልተከበረ ምንም ችግር አያመጣም፡፡

3. ከሚከተሉት ውስጥ ብዝሃ ባህል የማይገልፀው የቱ ነው?

    ሀ. ልዩነቶች ወደ ግጭትና ጦርነት ያመራሉ፡፡

    ለ. የተለያዩ የአለባበስ አይነቶች እና ጭፈራዎች መኖራቸው ውብ ነው፡፡

    ሐ. እያንዳንዱ ባህል ለህብረተሰቡ አንድ አንድ እሴቶችን ያበረክታል፡፡

    መ. የተለያዩ ባህሎች መኖር የጎብኝዎችን ትኩረት ይስባል፡፡

4. ከሚከተሉት ውስጥ የሰዎችን ባህል የሚያሳየው የትኛው ነው?

ሀ. የደስታ እና የሀዘን መግለጫ፡፡

ለ. የአለባበስ ስርዓት

ሐ. የአመጋገብ ስርዓት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

**ክፍል አራት. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ጻፉ፡፡**

1. ህጻናት በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ዋና ዋና መብቶች ዘርዝሩ፡፡
2. ስለ ፆታ እኩልነት ጥቅሞች ሁለት ነጥቦችን ጥቀሱ፡፡
3. በፆታ እኩል አለመታየት ዋነኛው ምንጭ ምንድን ነው?
4. የአድሎአዊነት የተለመዱ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው? ዘርዝሯቸው?

## ምዕራፍ አራት

# ጤናማ ማህበራዊ ህይወት

ምዕራፍ አራት፡ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የማማር ውጤቶች: ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡

- የጤናማ ማህበራዊ ግንኙነትን ጽንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ፤የጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት መገለጫዎችን ትገልፃላችሁ፤
- ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት ለማህበራዊ ስምምነት ያለውን ጠቀሜታዎች ዋጋ ትሰጣላችሁ፤
- ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነትን ታንፀባርቃላችሁ፤
- በጤናማ ማህበራዊ ግንኙነትን ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ነገሮችን ትለያላችሁ፤

መግቢያ

ተማሪዎች ይህ ምዕራፍ ከጤናማ ማህበራዊ ህይወት ትርጉም ጋር የምትተዋወቁበት ነው፡፡ በተጨማሪም ስለ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት መገለጫዎች ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም የጤናማ ማህበራዊ ህይወት መኖር ስላለው አስፈላጊነት በጥልቀት ያብራራል፡፡ በመጨረሻም በጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ነገሮችን ይዳስሳል፡፡

## 4.1 የጤናማ ማኅበራዊ ህይወት እሳቤዎች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ማለት ምንድን ነው?
- የጤናማ ማህበራዊ ህይወት መንገዶች ምንድን ናቸው?

እኛ ሰዎች ማህበራዊ ፍጡራን ነን። ስለዚህ ለጤንነታችንና ለደህንነታችን ዝምድና እና ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። ምንም እንኳን ጤናማ የሆነ እና የተመጣጠነ ምግብ መመገብ፣ በቂ እንቅልፍ ማግኘት እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ብንችልም ጤንነታችን የተሟላ ሊሆን ስለማይችል የማኅበራዊ ጤንነትን አስፈላጊነት መገንዘብና ከፍ አድርገን መመልከት ይኖርብናል። ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ሲባል ከሌሎች ጋር የመግባባትና ትርጉም ያለው ግንኙነት የመፍጠር ችሎታ ማለት ነዉ። በተጨማሪም ማኅበራዊ ችግሮች ሲያጋጥሙን ከሁኔታዎች ጋር እንዴት መላመድ እንደምንችል እና ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር ጋር ይዛመዳል።

ማኅበራዊ ህይወት በአእምሮአዊ፣ በአካላዊ ጤንነታችን እና በአጠቃላይ በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ለምሳሌ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ጥሩ የሀሳብ ልውውጥ ማድረግ፣ እርስ በርስ መከባበር፣ መቻቻል፣ ድጋፍ መጠየቅ፣ እርስ በርስ የመረዳዳት እና ችግሮችን በውይይት የመፍታት ልምድ ሊኖር ይገባል። እነዚህ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት መኖሩን ከሚጠቁሙ ነገሮች መካከል አንዳንዶቹ ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያውያንም እንዲህ አይነት ልዩ መገለጫዎች አሉን። ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መመሥረት፤ ጤንነታችንን፣ ደስታችንን እና አኗኗራችንን እንድናሻሽል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።



ምስል 4.1: ልጆች ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ሲኖራቸው

**ተግባር 4.1**

1. ከላይ ካለው ሥዕል ምን ተረዳችሁ?
2. ከላይ ያለው ሥዕል ከጤናማ ማህበራዊ ህይወት ጋር የተያያዘ ነው?

## የአማን ህይወት

አማን የ11 ዓመት ልጅ ሲሆን የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ወደ ብሔራዊ ሙዚየም የጉብኝት ጉዞ ነበር፡፡ ይህ ጉዞ የአካል ጉዳተኛ የሆነውን አማንን ጨምሮ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎችን ያጠቃልለ ነበር፡፡ በተጉዞም ላይ አማን በጣም ውስን የሆነ ማኅበራዊ ህይወት ስላለው በዙሪያው ካሉ ተማሪዎች ራሱን ያገል ነበር፡፡ይህም ከቅርብ ጓደኛው ቦና ጋር እስከተገናኙበት ግዜ ድረስ በጭንቀት እንዲሰቃይ አደረገው፡፡ የመንፈስ ጭንቀቱም ከባድ ለሆነ የጤና እክል አጋለጠው ፡፡ የቅርብ ጓደኛው ቦና ጋር አብረው ጥሩ ጊዜ በማሳለፋቸው እና እርስ በርስ በመማከራቸው የአማን ማህበራዊ ህይወት እና ከመንፈስ ጭንቀት ጋር ተያይዞ የመጣው የጤና ሁኔታ ጥሩ መሻሻል እያሳየ መጣ ፡፡ አማን ከቦና ጋር በመገናኘቱ ከጓደኞቹ እና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር የፍቅር፣ የእንክብካቤ እና የመተሳሰብ ስሜትን ለማዳበር አስችሎታል፡፡

**ተግባር 4.2**

1. ለአማን የመንፈስ ጭንቀት ምክንያቱ ምን ነበር?
2. የአማንን ማህበራዊ ህይወት በአዎንታዊ መልኩ የለወጡትን ነገሮች መጥቀስ ትችላላችሁ?

የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው

- ሌሎችን ማክበር፤
- የቤተሰብ እና የጓደኞች የመረዳዳት ትስስር መኖር፤
- ቸልተኛ ወይም ጠበኛ ከመሆን ይልቅ ጠንካራ ክህሎትን ማዳበር፤
- ለማኅበራዊ ህይወት እና ለግል የምንሰጠውን ጊዜ ሚዛናዊ ማድረግ፤
- በማኅበረሰቡ ውስጥ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር ተሳትፎ ማድረግ፤
- ከማኅበራዊ ሁኔታዎች ጋር መላመድ፤
- በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ራስን መሆን፤
- የጓደኝነትን ትስስር ማሳደግ እና መጠበቅ መቻል፤

- በጓደኝነት ውስጥ ገደብ በመፍጠር ግንኙነትን ማጠናከር እና ግጭትን በቀላሉ መፍታት፤
- በህይወት ደስተኛ መሆን፤

## 4.2. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ባህሪያት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

*ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ያለው ሰው ዋና ዋና ባህሪያትን ዘርዝሩ።



ምስል 4.2: የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ባህርያት

ጤናማ የሆነ ማኅበራዊ ህይወት በተለያዩ ገጽታዎች ሊገለፅ ይችላል። የሚከተሉት ደግሞ በተለምዶ ከሚታወቁት ባህርያት መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

- ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መመሥረት።
- የሌሎችን ሀሳብ መቀበል እና የራሱን አመለካከት መግለጽ፤
- መተባበር እና አብሮ መስራት፤
- እርስ በርስ መከባበር፤
- ተቻችሎ መኖር፤
- የግጭት አለመኖር፤
- ድጋፍ የመጠየቅ ባህል፤
- እርስ በርስ መረዳዳት፤
- ችግሮችን በውይይት መፍታት፤

## 4.3 የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- የጤናማ ማኅበራዊ ህይወት ዋነኛ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- ጤናማ ማኅበራዊ ህይወት አስፈላጊ እንደሆነ ታስባላችሁ? እንዴት?

ጤናማ የሆነ ማኅበራዊ ህይወት በጣም አስፈላጊ እና ለደህንነታችን አዎንታዊ አስተዋፅኦ አለው። ምክንያቱም ሁሉም ሰው መልካም ስብዕና እንዲኖረው

ስለሚረዳ ነው።

ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ጓደኞሞች እና ጥሩ ማኀበራዊ ህይወት ያላቸው ሰዎች የመቀራረብ እና የባለቤትነት ስሜት እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል።
- ስለ እኛ የሚያስቡ፣ አብረውን የሚደሰቱ እና  የሚያዝኑ ሰዎች እነዲኖሩን በማድረግ ጭንቀታችን እንዲቀንስ ይረዳል።
- አዕምሮአችንን ያዳብራል፣ሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅምን ያሳድጋል፣ እድሜያችንን ሊያራዝም ይችላል።
- አስቸጋሪ ነገሮች በሚያጋጥሙን ጊዜ ጓደኞሞች እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ ያደርጋቸዋልል።
- አንዳችን ለሌሎች ያለንን ጥሩ ግምት ይጨምራል።
- ሁላችን በአንድነት እንድንኖር ይረዳል።
- የግለሰቦችን ደህንነት እንዲሁም አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ዕድገታችንን  ያሻሽላል።
- በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ዕድገት እንዲሁም ጤና እና ማህበራዊ ህይወትን ያሻሽላል።

## 4.4. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**



* በጤናማ ማኀበራዊ ህይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩትን ነገሮች ዘርዝሩ?

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጤናማ ማህበራዊ ህይወት በጤንነታችን ላይ የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ ተፅዕኖ አለው። በጤናማ ማኀበራዊ ሕይወታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ከዚህ በታች የቀረቡት ናቸው።

- መገለል እና ጭፍን ጥላቻ፣
- የወላጅ እና የልጅ ግንኙነት ጤናማ አለመሆን፣
- የልጆች አስተዳደግ ዘይቤ እና ልምዶች፣
- የግልጽኝነት ባህል አለመኖር፣
- የቤተሰብ መፍረስ በመለያየት ወይም በፍቺ ምክንያት በአንድ ወላጅ የሚተዳደሩ በርካታ ቤተሰቦች እንዲኖሩ ያደርጋል፣
- የሥራ አጥ ቁጥር መጨመር፣
- ቸልተኝነት ወይም ጥቃት፣
- የወንጀል መበራከት፣



ምስል 4.3: ጤናማ ያልሆነ ማህበራዊ ህይወት

ተግባር 4.3

**ሦስት ተማሪዎችን የያዘ ቡድን አቋቁሙ እና በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው፦**

1. ጤናማ የሆነ የቤተሰብ ማኅበራዊ ህይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ምንድን ናቸው? በምን መንገድ ማሻሻል ይቻላል?
2. የግልፅኝነት አለመኖር በማህበራዊ ህይወት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል? አብራሩ::
3. በመለያየት ወይም በፍቺ ምክንያት የቤተሰብ መፍረስ አሉታዊ ተፅእኖ ያለው ይመስላችኋል? ተወያዩበት::
4. መገለልና ጭፍን ጥላቻ ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን እንዴት እንደሚጎዱ በዝርዝር አብራሩ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት አብረው የሚኖሩ ማህበራዊ ፍጥረታት ናቸው:: አንዳቸው ከሌላው ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል:: ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ከሚገለፅባቸው ባህሪያት መካከል አንዳንዶቹ፡- ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት እና ከጓደኞች ወዘተ ጋር ጠንካራ ግንኙነት መመስረት፤የሌሎችን ሀሳብ መቀበል፤ ከሌሎች ጋር መተባበር፤ መቻቻልን ማሳየት፤ እርስ በእርሳችሁ መረዳዳት እና ችግሮችን በውይይት መፍታት ናቸው:: ጤናማ ማህበራዊ ህይወት በግለሰቦች አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ ያሳድራሉ:: በዚህም ምክንያት ጤናማ ማህበራዊ ህይወት የግለሰቦችን አኗኗር ያሻሽላል:: ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ነገሮች መካከል፡- መገለል፣መቻቻል እና የግልፀኝነት አለመኖር ጥቃት ወዘተ ናቸው::

**ቁልፍ ቃላት**

- ✓ **ቁጡነት**፡- በቆራጥነት እና በጉልበት አንድ ነገር የማድረግ ባህሪ ነው፡፡
- ✓ **ድብርት**፡ በስሜት፣ በአስተሳሰብ እና በድርጊት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር የተለመደ እና ከባድ የሆነ የአዕምሮ በሽታ ነው ፡፡
- ✓ **ክብር**፡- በሌሎች ዘንድ አክብሮት የማግኘት ባሕርይ ወይም ሁኔታ ነው፡፡
- ✓ **ቻልተኛ**፡- ያለ ምንም ተቃውሞ፣ፈጣን ምላሽ ባለመስጠት የሚሆነውን ወይም ሌሎች የሚያደርጉትን መቀበል ወይም መፍቀድ፡፡
- ✓ **ጭፍን ጥላቻ**፡ "አንድን ሰው ወይም ነገር፣ በእውነተኛ ተሞክሮ ላይ ሳይመሰረት ለሰው ወይም ለነገር ያለን መጥፎ ስሜት" ነው፡፡
- ✓ **ማህበራዊ ህይወት**፡- ከሌሎች ጋር ለምሳሌ ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች፣ ከማህበረሰቡ አባላት እና እንግዶች ጋር ያለን ትስስር ማለት ነው፡፡

**የምዕራፉ የማጠቃለያ መልመጃዎች**

**እነዚህን የማጠቃለያ ጥያቄዎች ስሩ.**

**ክፍል አንድ: ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ሰዎችን ከሌሎች ጋር የመገናኘትና ትርጉም ያለው ግንኙነት የመመሥረት ችሎታ ነው ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡
2. ሰዎች ጤናማ ህይወት ለመኖር ሲሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት የሚመሰርቱ ማህበራዊ ፍጥረታት ናቸው፡፡
3. በማህበራዊ ህይወት እና በግለሰብ አካላዊ ደህንነት መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም፡፡

4. ከጓደኞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መገንባት ማህበራዊ ህይወትን ሊያሻሽል ይችላል፡፡
5. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ሁሉም ሰው ሊኖረው የሚገባ መልካም ስብዕና ነው፡፡

**ክፍል ሁለት: ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የቤተሰብን ጤናማ ማህበራዊ ህይወት የሚገልጸው የትኛው ነው?
   ሀ. እርስ በርስ መከባበር
   ለ. ለብቻ መኖር
   ሐ. እርስ በርስ መጨቃጨቅ
   መ. ችግሮችን በሃይል መፍታት
2. ከሚከተሉት ውስጥ ማህበራዊ ህይወት ጤናማ የመሆን አመልካች የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ቁጡ ባህሪ ያለው
   ለ. ሌሎችን አለማክበር
   ሐ. ቸልተኛ መሆን
   መ. ማህበራዊ ሁኔታዎችን መላመድ
3. ከሚከተሉት ውስጥ ጤናማ ማህበራዊ ህይወታችን ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማያሳድረው የትኛው ነው?
   ሀ. መገለል
   ለ. ቸልተኝነት
   ሐ. ሥራ አጥነት
   መ. አክብሮት ማሳየት
4. ስለ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነት ከሚከተሉት ውስጥ እውነት የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የጭንቀት መጨመር፡፡
   ለ. ለሌሎች አሉታዊ ስሜት መኖር፡፡
   ሐ. የእርስበርስ የመደጋገፍ ባህል መጨመር፡፡
   መ. ሰዎች አብረው እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡

**ክፍል ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልሶችን ጻፉ፡፡**

1. የጤናማ ማህበራዊ ህይወትን ጠቀሜታን ግለጹ፡፡
2. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት የተወሰኑ ባህሪያትን ዘርዝሩ፡፡
3. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን አብራሩ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

# መተባበር እና በቡድን መስራት

ምዕራፍ አምስት: መተባበር እና በቡድን መስራት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች: ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ :

- መተባበር እና በቡድን መስራት ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት ትችላላችሁ::
- በማህበረሰባችሁ እና በት/ቤታችሁ ዘንድ ያለውን የመተባበር እና በቡድን የመስራት ባህል ትለያላችሁ::
- ለመተባበር እና በቡድን መስራት መረሆች ዋጋ ትሰጣላችሁ::
- የመተባበር እና በቡድን መስራት ክህሎቶችን ትገልፃላችሁ::
- የመተባበር እና በቡድን የመስራት ጠቀሜታን ማስረዳት ትችላላችሁ::

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የመተባበር እና በቡድን የመስራትን ጽንሰ-ሃሳቦች ጠቅለል ባለ መልኩ ያስረዳል:: የመተባበር እና በቡድን መስራት ባህልን በኢትዮጵያ ለምሳሌ እንደ ደቦ (ጂጊ)፣እድር፣እቁብ እና ሌሎች የትምህርት ቤት ተግባሮችን በዝርዝር ያስረዳል:: በተጨማሪም የመተባበር እና በቡድን መስራት መርሆችን ይዘረዝራል:: ከዚያም ባሻገር ቅን-አሳቢነት፣ ተግባቦት፣ አደረጃጀት፣ በጥልቀት ማሰብ፣ መላመድን/ማላመድን፣ ክርክር፣ ጊዜ ቆጣቢነት እና ችግር ፈችነት የመሳሰሉትን የመተባበር እና በቡድን መስራት ክህሎቶች በትኩረት ይገልፃል:: በመጨረሻም ምዕራፉ የመተባበር እና በቡድን የመስራት ጠቀሜታን አጉልቶ ያሳያል::

## 5.1 መተባበር እና በቡድን መስራት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* በክፍል ውስጥ ቡድን አላችሁ?

የመተባበር እና በቡድን የመስራት ጽንሰ ሀሳቦች ለጋራ ግብ አብረው የሚሰሩ ሰዎችን ያካትታል። ይህ የሚሆነው በቡድኑ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች ሲኖሩ ነው። የቡድን ሥራና መተባበር በተናጠል ለማከናወን አስቸጋሪ የሆኑ ሥራዎችን ቀላል ከማድረጉም በላይ ሰዎች ስራቸውን በብቃት እንዲያከናውኑ ይረዳቸዋል።

የሚከተሉት ዋና ዋና ነገሮች ለመተባበር እና ለቡድን ስራ ያስፈልጋሉ።

1. ቡድኑን ለመርዳት ብዙ ስራ የሚሰሩ ግለሰቦች፣
2. በቡድን አባላት መካከል የጓደኝነት ስሜት፣
3. የቡድን መሪዎች ወይም አስተባባሪዎች፣
4. የጋራ ፍላጎት ወይም ግብ፣

ተግባር 5.1

1.የመተባበር እና በቡድን የመስራት ዋና ዋና መሰረታዊ ሀሳቦችን ጥቀሱ።

2.በአንድ የተወሰነ ተግባር ላይ በግል እና በቡድን መስራት ያለውን ጥቅም አወዳድሩ።

## 5.2. የመተባባር እና የቡድን ሥራ ባህል በማህበረሰብ እና በትምህርት ቤት ውስጥ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

*በማህበረሳባችሁ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ቡድኖችን መጥቀስ ትችላላችሁ?

### 5.2.1. በማህበረሰብ ውስጥ:

እኛ ኢትዮጵያውያን በበርካታ ቡድኖች በጋራ በመተባበር ስሜት አብረው የመሥራት ረጅም ታሪክ አለን። እነዚህ ቡድኖች በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የራሳቸው ስምና አሰራር አላቸው። ሰዎች እነዚህን የጋራ ባህላዊ ተቋማት ለተለያዩ ዓላማዎች ይጠቀሙባቸዋል። ለምሳሌ:-

1. ደቦ (ጂጊ) :- ብዙ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የሚጠቀሙበት የቡድን ሥራ ነው። በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን በእርሻና በመኸር ወቅት አብረው በጋራ ይሰራሉ። እንዲህ ዓይነቱ አገር በቀል ልማድ በመላ አገሪቱ በጣም የተለመደ ነው። በግለሰቦች መካከል ያለውን ጓደኝነት ማጠናከር፣ እርስ በርስ መደጋገፍ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ሥራዎችን ማጠናቀቅን ጨምሮ በርካታ ጥቅሞች አሉት። አካሄዶቹ ብዙውን ጊዜ ለእያንዳንዱ አባል ስራ ገንዘብ ከመክፈል ይልቅ

በጋራ በመስራት ስራን በአጭር ጊዜ እና በጥራት ለማከናወን ያስችላል። ከዚህም በላይ በማኅበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ ተግባር ማከናወን የማይችሉ ሰዎችን ለመደገፍ ይረዳል።



ምስል 5.1. ደቦ/ጂጊ/ በማህበረሰቡ ውስጥ

2. እድር: እንደ ሞት ባሉ ድንገተኛ ሁኔታዎችና የተለያዩ ችግሮች በሚገጥሙበት ወቅት የሚውል ገንዘብና ሌሎች ግብአቶችን ለማሰባሰብ በጎረቤቶች ወይም በሥራ ባልደረቦች መካከል የሚቋቋም ማህበር ነው። እድር በአንድ አካባቢ ተባብረው የሚኖሩ ሰዎች በሚገባ የሚያደራጁት ማህበር ነው። በአባላቱ በተወከሉት መሪዎች አማካኝነት ጥብቅ የሆነ አሠራሮችን ይከተላል።

## 5.2.2. በትምህርት ቤት ውስጥ - የቡድን ሥራ

ቡድን ወይም በቡድን መስራት በመተባበር የመማር ስልትን ያመለክታል። ይህ ሁኔታ ተማሪዎች አብረው ሲሆኑ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ሁኔታ ነው። ተማሪዎች እውቀታቸውን፣ ችሎታቸውንና ተሞክሮዎቻቸውን እንዲያካፍሉ ይረዳቸዋል። እያንዳንዱ ተማሪ ለቡድኑ የተሻለ አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅበታል።



ምስል 5.2. በቡድን መስራት በክፍል ውስጥ

ተግባር 5.2

1. በማህበረሰብ እና በትምህርት ቤት ውስጥ መተባበር እና በቡድን የመስራትን ባህል አስፈላጊነት ላይ ተወያዩ።
2. በእናንተ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ደቦ ያሉ ቡድኖችን በተመለከተ የእናንተን ተሞክሮ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ።
3. በማህበረሰባችሁ ውስጥ በጣም የተለመዱ እንደ ደቦ ያሉ የቡድን ሥራ ዘዴዎችን ሚና በክፍል ውስጥ ከቡድናችሁ ጋር አሳዩ።

## 5.3. የመተባበር እና በቡድን መስራት መርሆዎች



**የማነቃቂያ ጥያቄ**

*የእናንተን ቡድን አባላት ስም ልትጠቅሱ ትችላላችሁ?

መተባበር እና በቡድን መስራት ተለይተው የሚታወቁ የተለያዩ መርሆዎች አሏቸው። እስቲ አንዳንዶቹን እንመልከት።

1. እርስ በርስ መደጋገፍ - ሁሉም የቡድን አባላት ብቻቸውን ከመሥራት ይልቅ በጋራ መስራት በሚያስገኛቸው የጋራ ጥቅሞች ሊያምኑ ይገባል።
2. የግለሰብ ኃላፊነት - በቡድን ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ ከቡድኑ የሚጠበቅበትን ተግባር መፈፀም አለበት።
3. የቡድን ተግባራዊነት- የቡድኑ ተግባራዊነት የእያንዳንዱ አባል አስተዋፅኦ ውጤት ነው።
4. የተግባቦት ክህሎት፡- መግባባት ለቡድኑ ውጤታማነት ቁልፍ መሳሪያ ነው። በአባላቱ መካከል እምነት የሚገነባ ከመሆኑም በላይ በእጃቸው ላይ ባሉ ተግባራት ላይ ውሳኔ እንዲወስኑ ያስችላቸዋል።
5. አበረታች መስተጋብር: አባላት ተመሳሳይ ግብ ላይ ለመድረስ የሌሎችን ጥረት ማገዝ፣ ማበረታታትና መደገፍ አለባቸው።

ተግባር 5.3

1. በየቡድናችሁ ስለ መተባበርር መርሆዎች ተወያዩ።
2. የቡድናችሁን ተሞክሮ እና እያንዳንዱ አባል ለቡድኑ ውጤታማነት እንዴት አስተዋጽኦ እያደረገ እንዳለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።

## 5.4 የመተባበር እና በቡድን መስራት ክህሎት

### 5.4.1 የሌሎችን ሀሳብ አና አመለካከት የመቀበል ዝግጁነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* እናንተ በቡድናችሁ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ሀሳብ ለማዳመጥ ፈቃደኛ ናችሁ?

የሌሎችን ሀሳብ እና አመለካከት የመቀበል ዝግጁነት ማለት የሌሎችን ሀሳብ እና አመለካከት በቅንነት ተቀብሎ ማስተናገድ ተብሎ ሊብራራ ይችላል:: ይኸውም የኛን ሀሳብ የሚቃረን አመለካከት ቢኖራቸውም እንኳ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆንን ያካትታል:: በተጨማሪም የሌሎችን ሀሳብ እና አመለካከት የመቀበል ዝግጁነት ተጨባጭ የሆነ መረጃ ላይ በመመስረት ሌሎችን የማሳመን ክህሎት እና የቡድን አባላትን ትብብር ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ እውነታን በቅንነት መፈለግ ማለት ነው::

የሌሎችን ሀሳብ እና አመለካከት የመቀበል ዝግጁነት ማለት ስለቡድኑ ግልጽ ያልሆኑ እቅዶች፣ አስተያየቶች፣ ግቦችና ተግባራት ጥያቄዎችን መጠየቅን ያካትታል:: ይህም በቡድኑ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ይረዳል:: በመሆኑም አባላቱ የተሰጣቸውን ተግባራት በጋራ መንፈስ እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸውን የመቀበልና የመቃወም ክህሎት ማዳበርን ይጨምራል::

**ተግባር 5.4**

1. ከቡድናችሁ ጋር የሌሎችን ሀሳብ አና አመለካከት ስለ መቀበል ዝግጁነት ጽንሰ-ሀሳብ ተወያዩ?
2. ሃሳባችሁን በግልፅ ለማስረዳት ወይም ሌሎችን ለማዳመጥ ፈቃደኛ ናችሁ? እስኪ በክፍል ውስጥ ተሞክሮአችሁን አጋሩ?

### 5.4.2. ተግባቦት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

ለጓደኞቻችሁ መረጃ የምትሰጡበት ወይም ከጓደኞቻችሁ መረጃ የምትቀበሉበት መንገድ ምንድን ነው?




ምስል 5.3. የእርስበርስ ተግባቦት

ተግባቦት መረጃን የመስጠት፣ የመቀበል እና የማጋራት ድርጊት ነው። ተግባቦት መረጃን መለዋወጥ ማለት ነው። ተግባቦት መናገርን፣ መፃፍን፣ መረጃ ማዳመጥን እና/ወይም ማንበብን ያካትታል። ተግባቦት በተለያዩ ስልቶች ማለትም በቃል፣ በምልክት እና በዕይታ መልክ ሊተገበር ይችላል።

በተጨማሪም ተግባቦት በአባላት መካከል የጋራ መንፈስ እንዲኖር የሚያደርግ የቡድን ሥራ ክህሎት ነው። የጋራ ግብ ላይ ለመድረስ በአባላቱ መካከል የጋራ መግባባት እንዲኖር አስተዋጽኦ ያደርጋል። ጥሩ ተግባቦት እንዲኖር በጥሞና ማዳመጥ፣ በግልጽነት መናገርንና የተሳታፊዎቹን የተለያየ አመለካከት ማክበርን ይጠይቃል።

**ተግባር 5. 5**

1. ስለተግባቦት ጽንሰ ሀሳብ ተወያዩ።
2. በቡድን በመሆን ሥራዎችሁን ስትሰሩ ቡድናችሁ ያጋጠመውን የተግባቦት ተግዳሮት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።

### 5.4.3. አደረጃጀት



**የማነቃቂያ ጥያቄ**

*አደረጃጀት የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወዲያው ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ነገር ምንድን ነው?

አደረጃጀት ማለት በአንድ ላይ የሚሰሩ የሰዎች ስብስብ ማለት ነው።አደረጃጀት የጋራ ግባቸውን ለማሳካት ሰዎች በአንድ ላይ በመስራታቸው ምክንያት የሚፈጠር ነው።

በሌላ መልኩ አደረጃጀት የመተባበር እና በቡድን የመስራት ክህሎት እንደመሆኑ መጠን የቡድኑን ውጤታማነት ሊደግፉ የሚችሉ ሃሳቦች፣ ሁነቶች፣ ሀብቶች፣ እና መረጃዎች ስብስብ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል።



ምስል 5.4. የነገሮችን አደረጃጀት ያሳያል

ተግባር 5. 6

1. በቡድናችሁ ውስጥ ስለአደረጃጀት ጽንሰ-ሀሳቦች ተወያዩ።
2. ከቡድናችሁ ጋር በመሆን ሞዴል መኪና ለመሰራት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች በሙሉ አደራጁ (የቤት ስራ)።

### 5.4.4. ክርክር



**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* ክርክር ምንድን ነው?

**"ክርክር"፡-** በስብሰባ ላይ አንድ የተለየ ጉዳይን አስመልክቶ የሚደረግ መደበኛ ውይይት ተደርጎ ሊታይ ይችላል። ተከራካሪዎች ተፎካካሪዎቻቸውን ወይም ተመልካችን ለማሳመን ሙከራ የሚያደርጉበት መንገድ ነው።



ምስል 5.5. ቡድኖች በክርክር ላይ

የክርክር ዓላማ ከኛ ሀሳብ ተቃራኒ የሆነን ሰው ትክክል እንደሆንን ማሳመን ነው። ክርክር በድምፅ ብልጫ አለያም በተከራካሪዎቹ መካከል ባለው ስምምነት ያበቃል። ክርክር ተከራካሪዎቹ የሚከተሉትን ጥብቅ የሥነ ምግባር ደንቦች ይከተላል።

ክርክር ለቡድን ስራ እና ለመተባበር አስፈላጊ ክህሎት ነው። በቡድኑ አባላት መካከል አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ ነገሮችን ለመቆጣጠር ይረዳል። በተጨማሪም አባላቱ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉት የተወሰኑ ግራ መጋባቶችን ግልጽ ያደርጋል።

ተግባር 5.7

1. በቡድናችሁ ስለ ክርክር ጽንሰ-ሀሳብ ተወያዩ።
2. አንድ ርዕሰ ጉዳይ ምረጡና አስተማሪያችሁ ከሚያደራጃችሁ ቡድን ጋር በመሆን በክፍል ውስጥ ተከራከሩ።

## 5.4.5. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

* በቤታችሁ ውስጥ የምትከተሉትን የጥናት መርሃ ግብር መናገር ትችላላችሁ?

ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ማለት ተግባሮችን መሰረት በማድረግ ጊዜን በአግባቡ ከፋፍሎ የመጠቀም ሂደት ሲሆን ስራዎችን በቅደም ተከተል አስቀምጦ ለማከናወን ይረዳል፡፡ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ስራዎችን በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ ይረዳል፡፡

ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም እንዲኖረን የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች መከተል አለብን፡-

- ልናሳካቸው የምንፈልጋቸው ግቦች፣
- በአስቸኳይነታቸው እና በአስፈላጊነታቸው ላይ ተመሥርተን ለሥራዎች ቅድሚያ መሰጠት፣
- ለእያንዳንዱ ተግባር እቅድ ወይም የጊዜ መርሃ ግብር ማስቀመጥ፣
- ማቀድ እና
- በእቅዳችን መሰረት ስራዎችን መስራት፤



ምስል 5.6. የጊዜ አጠቃቀምን ያሳያል

**ተግባር 5.8**

1. በቡድናችሁ ጊዜን በአግባቡ ስለ መጠቀም ጽንሰ-ሀሳብ ተወያዩ፡፡
2. በቤታችሁ የምታከናውኑትን ተግባራት በመዘርዘር እና ለእያንዳንዱ ተግባር ምቹ ጊዜን በመመድብ ሠርቶ በማሳየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## 5.4.6 የመተባበር እና በቡድን መስራት ጠቀሜታ

**የማነቃቅያ ጥያቄ**

- የመተባበር እና በቡድን የመስራትን ፅንስ ሀሳቦች ልታብራሩ ትችላላችሁ?

መተባበር እና በቡድን መስራት በጣም ጠቃሚ ነው። ልምድን፣ ዕውቀትን፣ ክህሎትን ለመጋራት እና በቡድኑ አባላት መካከል መግባባትን ለመፍጠር ይረዳል። ከተለያየ ዳራ እና ልምድ የሚመጡ ሰዎች በጋራ እንዲሰሩና እንዲተባበሩ ያደርጋል። እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ዕውቀትን፣ ተሰጥዖን፣እና ክህሎትን ለቡድኑ ሊያበረክት ይችላል። እንዲሁም ችግሮቻቸውን ለመፍታት እና ከጋራ ግባቸው ለመድረስ አዳዲስ ሀሳቦችን የሚጠቁሙበት ነው።
በትምህርት ቤት ውስጥ በትብብር መማርና መስራት በተማሪዎች መካከል በራስ መተማመንን፣ ለራስ ዋጋ መስጠትን ለማዳበር እንዲሁም የአቻ ለአቻ ግንኙነቶችን ለማበረታታት ይጠቅማል። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ በአንዳንድ አስቸጋሪ ፅንሰ ሀሳቦች ዙሪያ እንዲወያዩ እና እንዲገነዘቡቸው ያደርጋል። መተባበር ነገሮችን ለማደራጀት ምቹ ሁኔታን የፈጥራል።



ምስል 5.7. የመተባበር እና በቡድን መስራት ጠቀሜታ

**ተግባር 5.9**

1. መተባበር እና በቡድን መስራት ስላለው ጠቀሜታ ተወያዩ።
2. ለእናንተ ይበልጥ ጠቃሚ የሆነው የትኛው ነው፤
   የክፍል ስራ ለየብቻ መስራት ወይስ በቡድን መስራት?
   ተሞክሮአችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ብታካፍሉስ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

መተባበር እና በቡድን መስራት የጋራ ግብን ለማጠናቀቅ ይረዳል፡፡ በአንድ ሰው ለማከናወን አስቸጋሪ የሆኑ ተግባራትን ቀላል ያደርጋል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን በበርካታ ቡድኖች የመሳተፍ እና የመተባበር የረጅም ጊዜ ታሪክ አለን፡፡ ለምሳሌ ደቦ (ጅጊ) እና እድር ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ መተባበር እና በቡድን መስራት ከአብሮነት ውጤታማነት ጋር በተገናኘ የራሳቸው የሆነ መርሆዎች አላቸው ፡፡ እነሱም የሌላን ሰው አስተሳሰብ ወይም ሀሳብ መቀበል፣ ተግባቦት፣ አደረጃጀት፣ ሂሳዊ አስተሳሰብ፣ መላመድ፣ ክርክር፣ የጊዜ አጠቃቀም እና ችግር ፈቺነት ክህሎቶች ናቸው፡፡ መተባበር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ እውቀታቸውን፣ ችሎታቸውን እና ክህሎታቸውን ለቡድኑ ማበርከት ይችላሉ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ✓ **መተባበር**፡- አንድን ነገር ለማሳካት ወይም ለመስራት ከሌላው ሰው ወይም ቡድን ጋር አብሮ መስራት
- ✓ **የእርስ በርስ መስተጋብር**፡- ማለት በጋራ ወይም በግል ሌላውን የመደገፍ ተግባር ወይም ተፅዕኖ ነው፡፡
- ✓ **አደረጃጀት**፡- የአንድን ክስተት ወይም ተግባር የተለያዩ ክፍሎችን የማቀድና የማዘጋጀት ተግባር ወይም ሂደት ነው፡፡
- ✓ **ክርክር**፦ በሰዎች መካከል የሚደረግ የሀሳብ ልውውጥ ነው፡፡ ሰዎች ስለ አንድ ነገር ያላቸውን የተለያየ አመለካከት የሚገልፁበት ውይይት ነው፡፡

### የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች

**ክፍል አንድ: ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. መተባበር እና በቡድን መስራት ለአንድ ሰው አስቸጋሪ የሆኑ ተግባራትን ለመከወን የበለጠ ተገቢ ነው፡፡
2. ተግባቦት ለተቀባዩ መረጃ የመስጠት ተግባር ብቻ ነው፡፡
3. የሌሎችን ሀሳብ እና አመለካከት የመቀበል ዝግጁነት ማለት የሌሎችን ሀሳብ በቅንነት ለመቀበል ፈቃደኛ የመሆን ክህሎትን ያጠቃልላል፡፡
4. ክርክር ተከራካሪዎቹ ሊከተሏቸው የሚገቡ ጥብቅ የስነምግባር ደንቦች አሉት፡፡

**ክፍል ሁለት: በዓምድ "ለ" ስር የተሰጡትን የመተባበር እና በቡድን የመስራት ክህሎቶች በዓምድ"ሀ" ስር ካሉት ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ::"**

| ዓምድ'ሀ' | ዓምድ 'ለ' |
|---|---|
| 1. ከአዲስ ሁኔታዎች ጋር ራስን ለማስማማት አንድን ነገር የመቀየር ችሎታ | ሀ/ ክርክር |
| 2. ነገሮችን በተገቢ ቅደም ተከተል ማስቀመጥ | ለ/ መላመድ |
| 3. የመረጃ ልውውጥ | ሐ/ አደረጃጀት |
| 4. በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ መደበኛ ውይይት ማድረግ | መ/ ተግባቦት |

**ክፍል ሦስት: ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ ::**

1. ለአደጋ ጊዜ ገንዘብ ለማሰባሰብ በጎረቤቶች መካከል የሚቋቋም ማህበር የትኛው ነው?
   - ሀ. ደቦ
   - ለ. እቁብ
   - ሐ. እድር
   - መ. ጂጊ
2. ከሚከተሉት ውስጥ የቡድን ሥራ መርህ ያልሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. እርስበርስ መደጋገፍ
   - ለ. ሌሎቹን መጉዳት
   - ሐ. የግለሰብ ኃላፊነት
   - መ. የተግባቦት ክህሎት
3. ከሚከተሉት ውስጥ መፍትሔ የማፈላለጊያ ተግባር የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
   - ለ. ጥልቅ አስተሳሰብ
   - ሐ. ችግር ፈቺነት
   - መ. የሌሎችን ሀሳብ የመቀበል ዝግጁነት

**ክፍል አራት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልሶችን ጻፉ::**

1. የመተባበር እና በቡድን የመስራትን ጠቀሜታ ጥቀሱ::
2. ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም ሂደቶች ምንድን ናቸው?
3. ችግራችሁን በምትፈቱበት ጊዜ ልትከተሏቸው ስለሚገባችሁ ቅደም ተከተሎች ተወያዩ::

# ምዕራፍ ስድስት

# ብዝሃ-ባህል

ምዕራፍ ስድስት: ብዝሃ-ባህል

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች: ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ :

- የብዝሃ-ባህልን ትርጉም መግለፅ ትችላላችሁ፣
- ብዝሃ-ባህል ማስተናገድ ያለውን ጠቀሜታ ማብራራት ትችላላችሁ፣
- የማህበረሰባችሁን ብዝሃ-ባህል ማድነቅ ትችላላችሁ፣
- ብዝሃ-ባህልን የማስተናገጃ መንገዶች ማስረዳት ትችላላችሁ።

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ከብዝሃ-ባህል ጋር ያስተዋውቃችኋል። እንዲሁም ብዝሃ-ባህልን ማስተናገድ ስላለው ጠቀሜታ ግንዛቤ ይፈጥርላችኋል። ጎሳ፣ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ የአለባበስ ሁኔታ፣ ባህላዊ ሙዚቃ፣ ባህላዊ ምግብ፣ የሰርግ ባህል እና የመሳሰሉትን የብዝሃ ባህል መገለጫዎች በሰፊው ይዳስሳል። በመጨረሻም ብዝሃ ባህልን ማስተናገድ ያለውን ጠቀሜታ እና ብዝሃ ባህልን የማስተናገጃ መንገዶች ግንዛቤ ይሰጣል።

## 6.1 የብዝሃነት ምንነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ብዝሃነት ምን እንደሆነ ግለፁ፡፡
- የብዝሃ ባህል መሰረቶችን ባጭሩ ተወያዩ፡፡

"ብዝሃነት" ሰዎች ስለሚለያዩባቸው መንገዶች በሰፊው የሚገልፅ ሲሆን ይህም በግል እና በቡድን ደረጃ በሰዎች መካከል ያሉትን የሚታዩ እና የማይታዩ ልዩነቶችን ያጠቃልላል፡፡ ብዝሃነት በዘር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣እና በማህበራዊ ደረጃ ላይ ተመስርተው በተፈጠሩ ቡድኖች ውስጥ ያለ ልዩነት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ብዝሃነት “በግለሰቦች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያመለክት ሲሆን ይህም ሌላ ሰው ከራሱ የተለየ ነው ወደሚል አመለካከት ሊያመራ” ይችላል፡፡ ብዝሃ ባህል፣ የተለያዩ ሀሳቦች፣ አመለካከቶች እና እምነቶች ለተሻለ ማህበረሰብ ያለንን እይታ ያሳድጋል፡፡ የተለያዩ ባህሎች የተለያየ የትርጉሜ ሥርዓቶችን፣ እሴቶችን፣ እና ለጥሩ ህይወት ፅንስ ሀሳቦችን ይሰጡናል፡፡ ስለዚህ ስለ ዓለም ያለንን ግንዛቤ እናሰፋለን፡፡ በውጤቱም ብዝሃ ባህል አማራጮቻችንን እና ምርጫዎቻችንን ለማስፋት እንደ ጠቃሚ ምንጭ ይቆጠራል፡፡ የህይወት ራዕያችንን እና በማህበራዊ ህይወት ያለንን አርአያነት ያሰፋዋል እና ጥልቅ እውቀት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ የሀሳብ ልዩነት ስለ ተገለሉ ሰዎች የአኗኗር ዘይቤዎች እና የአለም እይታዎች በአዎንታዊ መልኩ ዋጋ ሊሰጣቸው የሚችሉበትን የታሪክ አማራጭ ይሰጣል፡፡



ምስል 6.1: የተለያዩ የኢትዮጵያ ህዝቦች

## 6.2. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ብዝሃ ባህል ዓይነቶች

ባህል የማንኛውም ማህበረሰብ አካል የሆኑ ምልክቶች፣ ቋንቋዎች፣ እምነቶች፣ እሴቶች እና ቅርሶች ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ባህልና ህብረተሰብ አይነጣጠሉም፡፡ ይህም ማለት ባህል ከሌለ ማህበረሰብ የለም ማህበረሰብ ከሌለ ደግሞ ባህል

የለም ማለት ነው። እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህል እና ልዩ አሰራር ስላለው፤ ይህም የብዝሃነት ምንጭ ነው። ዋና ዋናዎቹ ብዝሃ ባህል ዓይነቶች በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በባህላዊ አልባሳት፣ በባህላዊ ሙዚቃ፣ በባህላዊ ምግብ፣ የሰርግ ባህል ወዘተ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።

## 6.2.1. ጎሳ

**ጎሳ፡-** የጋራ ባህላዊ ወጎች ያላቸው የአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ አባል የመሆን እውነታ ነው። ጎሳ ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ የጋራ ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ሃይማኖት እና ማኅበራዊ አያያዝን መሠረት በማድረግ እርስበርስ የሚተዋወቁ ሰዎች ስብስብ ነው። ስለዚህ ጎሳ በዘር ወይም አንድ ሰው በሚኖርበት ማህበረሰብ ማንነት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል። ውስጣዊ ትስስር፣ የዝምድና እና የጋራ ስሜትን ይፈጥራል። የአንድ ጎሳ አባላት ከሌሎች ቡድን አባላት ይልቅ በደም ትስስር እርስ በርስ የተያያዙ መሆን አለባቸው። ስለዚህ ጎሳ የብዝሃ ባህል መሰረት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።

## 6.2.2. የባህል አልባሳት

የባህል ልብስ ማለት ባለፉት ዘመናት የየትኛውም ማህበረሰብ አባላት ተለይተው የሚለበሱት ልብሶች እና ጌጣጌጦች ስብስብ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አለባበስ ለዕለት ተዕለት ሕይወታችን አስፈላጊ ነገር ነው። በአለባበስ፣ ግለሰቦች የራሳቸውን ስሜት እና የማህበረሰባቸውን ማንነት መግለጽ ይችላሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች የራሳቸው የሆነ የባህል አለባበስ ዘይቤ አላቸው። ይህም ብዝሃነትን ያሳያል።



ምስል 6.3: የባህል ልብሶች በኢትዮጵያ

## 6.2.3. ባህላዊ ሙዚቃ

ሙዚቃ ከማንነታችን ጋር የተቆራኘ ነው:: የጋራ ማንነትን በመፍጠር ማን መሆናችንን እንድንገልጽ ይረዳናል:: አንዳንድ የጋራ የሆኑ ነገሮች ቢኖሩም የባህል ሙዚቃ በሁሉም ባህል የተለያየ ነው:: የባህል ሙዚቃ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም የባህል ልምዶችን የምናከብርበት፣ ሰዎች እርስበርስ የሚተሳሰሩበት፣ ማንነታቸውን የሚያገኙበት በተጨማሪም ግለሰቦች ቋንቋ እንዲማሩ ስለሚረዳ ነው::



ምስል 6.4: የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

## 6.2.4. ባህላዊ ምግብ

ባህላዊ አመጋገብ የምግብ አሰራርን፣ አመጋገብን እና የአቀራረብ ዘዴዎችን ያካትታል:: ኢትዮጵያውያን ባህላዊ ቅርሶቻቸውን በመጠበቅ ትልቅ ኩራት ይሰማቸዋል:: እያንዳንዱ የአገሪቱ ክፍል የየራሱ የባህል ምግቦች አሉት::



ምስል 6.5: የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግቦች

## 6.2.5. የሰርግ ባህል

ሰርግ ሁለት ሰዎች ( ማለትም አንድ ወንድ እና አንድ ሴት) በትዳር ውስጥ የሚዋሃዱበት ሥነ ሥርዓት ነው። የሰርግ ወጎች እና ልማዶች፣ በጎሳ፣ በሃይማኖቶች፣ በአገሮች እና በማህበራዊ መደቦች መካከል በጣም የተለያዩ ናቸው። በአብዛኞቹ የሠርግ ሥነ ሥርዓቶች ጥንዶች የጋብቻ ቃልኪዳን መለዋወጥ ወይም መተሳሰር፣ ስጦታም በማቅረብ (ለምሳሌ፡- ቀለበት፣ ጥሎሽ፣ አበባ፣ ገንዘብ፣ ልብስ፣ ከብት ወዘተ) እና በተከበሩ ወይም በታዋቂ ሰዎች የሚፈጸም ነው። በኢትዮጵያ እና በሌሎች የአለም ክፍሎች የተለያዩ የሰርግ ባህሎች አሉ። ይህም የብዝሃነት መሰረት ወይም መገለጫ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።



ምስል 6.6: የተለያዩ የሰርግ ባህሎች በኢትዮጵያ

## 6.3. ብዝሃ ባህል የማስተናገድ አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ የበርካታ ህዝቦች እና ባህሎች ሀገር ነች። እነዚህንና ሌሎች ብዝሃነቶችን ማቻቻል በሰላምና በመተባበር ለመኖር አስፈላጊ ነው። የተለየ የባህል መገለጫ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የራሳቸው የሆነ አስተዋፅኦ አላቸው። የብዝሃ ባህል መኖር ማለት የተለያዩ የአለባበስ ዘይቤዎች፣ ባህላዊ ምግቦች እና የባህል ውዝዋዜዎች እና የመሳሰሉት መኖር ማለት ሲሆን እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያን ውብ እና ማራኪ አድገዋታል። ይህም ደግሞ ብዙ ጎብኚዎችን በመሳብ የሀገራችንን ገቢ እንዲጨምር ያደርጋል።

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የባህል ቡድኖች አዲስ የፈጠራ ስራ እና ግኝቶች እንዲያዳብሩ ሊያግዝ ይችላል። ከዚህ ባለፈ ይህ ብዝሃነት ሀገራችንን የበለጠ ለመኖሪያ ምቹ ቦታ ያደርጋታል። ምክንያቱም የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የቋንቋ ክህሎት፣ አዲስ የአስተሳሰብ ዘይቤ፣ አዲስ እውቀት እና የተለያዩ ልምዶችን ስለሚያበረክቱ ነው። ባህሎቻችንን በእኩል ዓይን ስናይ የበለጠ

መጠቀም እንችላለን፡፡ በአለባበስ ዘይቤ፣ በጭፈራ/ውዝዋዜ፣ በባህላዊ ምግቦች፣ ወዘተ ያሉንን ልዩነቶች ማክበር አለብን፡፡ በባህል እኩልነት ስናምን እነዚህን እና ሌሎች የባህል ልዩነቶችን እናከብራለን፡፡ እርስ በርስ በመከባበር እንደ ድህነትና ኋላ ቀርነት ያሉ የጋራ ጠላቶቻችንን መታገል እና የአገራችንን እድገት ማፋጠን እንችላለን፡፡

**ተግባር 6.1 በቡድን መስራት:**
ብዝሃ ባህልን ማስተናገድ ስላለው ጠቀሜታ በቡድን ተወያዩ፡፡

## 6.4. ብዝሃ ባህልን የማስተናገጃ መንገዶች

ብዝሃ ባህልን ማስተናገድ የተለያዩ የባህል ቡድኖች በጋራ መኖር ማለት ነው፡፡ የሌሎችን ቋንቋ፣ ሃይማኖት እና የአኗኗር ዘይቤ በማክበር አብሮ መኖር ማለት ነው፡፡ ይህ ሁሉም ባህሎች ሃይማኖቶች እና ቋንቋዎች እኩል ናቸው በሚለው እምነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉም ሰው በእኩልነት ሊስተናገድ ይገባዋል፡፡ የብዝሃ ባህል ማህበረሰብ ሁሉም አባላት እርስ በርስ እስከ ተከባበሩ ድረስ በሰላም ይኖራሉ፡፡ ይህን በተግባር አለማዋል ማህበራዊ ሰላምን እና እንደ አንድ ማህበረሰብ በጋራ የመኖር ችሎታን በቀላሉ ሊያናጋ ይችላል፡፡ ብዝሃ ባህልን የማስተናገጃ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ለብዝሃ ባህል እውቅና መስጠት፤
- የራስን ባህል የበላይ ወይም የበታች አድርጎ አለመመልከት፤
- ልዩነቶችን ማክበር፤
- የግለሰቦችን ወይም የቡድን አኗኗርን እንደ ኋላ ቀር አድርጎ ከመመልከት መቆጠብ፤
- የተለያዩ ባህላዊ መገለጫዎች ትክክለኛነትን መቀበል እና ለአስተዋፅኦቻቸውን እውቅና መስጠት፤
- ሌሎች ባህሎች ለሚያቀርቡት ነገር ዋጋ መስጠት፤
- የሌሎችን ባህል ለማድነቅ ዝግጁ መሆን፤
- የተለያዩ ቡድኖችን አስተዋፅኦ ማበረታታት፤
- ሰዎች እራሳቸውን እና ሌሎችን እንዲያጠናክሩ እንዲሁም የራሳቸውን አድሎአዊነት የመተቸት ከፍተኛ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ማበረታታት፤ እና
- በልዩነት ውስጥ አንድነትን ለማምጣት ልዩነቶችን ማቻቻልና ማክበር፡፡

**ተግባር 6.2**

1. በማህበረሳባችሁ ውስጥ ስላሉት ብዝሃ ባህል የማስተናገጃ መንገዶች በቡድን ተወያዩ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ብዝሃነት፡- በዘር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ እና በማህበራዊ ሁኔታ ላይ በመመስረት በቡድን ውስጥ እና ከቡድን ውጭ ያለ ልዩነት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የተለያዩ ባህሎች ለግለሰቦች ትርጉም ያላቸው አማራጮችን ይሰጣሉ፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ልዩ ባህልና ልማዶች አሉት፡፡ ይህም የብዝሃነት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ የብዝሃ ባህል ዓይነቶች ጎሳ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህላዊ ልብስ፣ ባህላዊ ሙዚቃ፣ ባህላዊ ምግብ፣ የሰርግ ባህልን እና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡እነዚህን እና ሌሎች ልዩነቶችን ማቻቻል በሰላም እና በመተባበር ለመኖር አስፈላጊ ነው፡፡ የብዝሃ ባህል ማህበረሰብ ሁሉም አባላት እርስበርስ እስከተከባበሩ ድረስ በሰላም ይኖራሉ፡፡ ብዝሃ ባህልን ማስተናገድ፣ ለብዙ ባህሎች እውቅና የመስጠት፣ የራስን ባህል የበላይ ወይም የበታች አድርጎ የመመልከት ዝንባሌን የማስወገድ፣ ልዩነቶቹን የማክበር እና የተለያዩ የባህል አገላለጾች እና አስተዋጾዎች ትክክለኛነትን መቀበልን ይጠይቃል፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ✓ **ማስተናገድ:** ልዩነቶች ቦታ እንዲኖራቸው መፍቀድ፡፡
- ✓ **ብዝሃነት:** በሰዎች የተለያየ አመጣጥ ምክንያት ያሉ ልዩነቶች ማለት ነው
- ✓ **ጎሳ**፡ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የጋራ ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ሃይማኖት እና ማኅበራዊ አያያዝ መሠረት በማድረግ እርስበርስ የሚተዋወቁ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡
- ✓ **ሰርግ:** ሁለት ሰዎች (ማለትም አንድ ወንድ እና አንድ ሴት) በትዳር ውስጥ የሚዋሃዱበት ሥነ ሥርዓት ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች

**ክፍል አንድ: ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስሕተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. ብዝሃነት በሰዎች አመጣጥ መሠረት በቡድን ውስጥ እና ከቡድን ውጭ ያለ ልዩነት ነው።
2. ገናና የሆኑ ባህላዊ ቡድኖች ከአናሳዎቹ የበለጠ ተቀባይነት አላቸው።
3. ባህል እና ማህበረሰብ የማይነጣጠሉ ናቸው።
4. በአለም ላይ ባህል የሌለው ማህበረሰብ ሊኖር ይችላል።
5. ቋንቋ በሰዎች መካከል የመግባቢያ መሳሪያ ነው።

**ክፍል ሁለት: በ"ሀ" ምድብ የተሰጡትን ማብራሪያዎች በተመሳሳይ ከ "ለ" ምድብ ከተሰጡት ፅንስ ሀሳቦች ጋር አዛምዱ፤-**

| ምድብ ሀ | ምድብ ለ |
|---|---|
| 1.ተለይተው የሚታወቁ ሰዎች የሚለብሷቸው ልብሶች | |
| 2. ሰዎች የሚያመልኩበት የእምነት ሥርዓት | |
| 3.የምግብ አዘገጃጀት፣ የአመጋገብ እና የአቀራረብ ዘዴዎች | |
| 4.የአንድ የተወሰነ ማህበራዊ ቡድን አባል መሆን | |
| 5.የተወሰነ ቡድን የሚጠቀመው የግንኙነት መሳሪያ | |

**ክፍል ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልሶችን ጻፉ።**

1.ብዝሃ ባህልን ለማስተናገድ የሚያስችሉ መንገዶችን ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ።
2.ብዝሃ ባህልን የማክበር አስፈላጊነት ምን እንደሆነ አስረዱ።